# በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
# የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

## የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የድጋፍ አሰጣጥና የዕድገት ደረጃ ሽግግር ማንዋል

## (የጸደቀ)


**አዘጋጆች ፡ -**

1. **አቶ ጌታሁን ሞላ**
2. **ወ/ሮ ቅድስት አምዴ**


**ጥር/2018 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

ማውጫ ..................................................................................................................................... ገጽ


መግቢያ ........................................................................................................................................ 1
ክፍል አንድ ................................................................................................................................... 2
ጠቅላላ .......................................................................................................................................... 2
1.1 አጭር ርዕስ ............................................................................................................ 2
1.2 ትርጓሜ ................................................................................................................... 2
1.3 የተፈጻሚነት ወሰን ................................................................................................. 3
1.4 የማንዋሉ ህጋዊነት ................................................................................................. 3
1.5 የማኑዋሉ ዓላማ ...................................................................................................... 3
1.6 የማኑዋሉ አስፈላጊነት ............................................................................................ 4
1.7 የማኑዋሉ መርሆዎች ............................................................................................... 5
1.8 የማኑዋሉ ተጠቃሚዎች ............................................................................................ 5
1.9 የሚጠበቅ ውጤት ..................................................................................................... 5
ክፍል ሁለት .................................................................................................................................. 6
የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ እና የሽግግር መስፈርቶች .......................................................... 6
2.1 የኢንተርፕራይዝ ዕድገት ደረጃ ................................................................................... 6
2.2 የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር ዋና ዋና መስፈርቶች ..................................... 9
2.3 ለኢንተርፕራይዞች በየዕደገት ደረጃቸው የሚሰጡ የድጋፍ ማዕቀፎች .......................... 23
2.3.1 በጀማሪ ደረጃ የሚሰጥ ድጋፍ ...................................................................................... 23
2.3.2 በማደግ ደረጃ የሚሰጥ ድጋፍ ...................................................................................... 24
2.3.3 በመብቃት ደረጃ ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡ ድጋፎች ..................................... 24
ክፍል ሦስት ................................................................................................................................. 25
የፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ............................................................................... 25
3.1 የፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ........................................................................... 25
ክፍል አራት ................................................................................................................................. 30
የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ......................................................................................................... 30
4.1 የሚከናወኑ የክትትል፣ ግምገማ እና ግብረ መልስ ስራዎች ........................................ 31
4.2 ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቶች ................................................................................. 31
ክፍል አምስት ............................................................................................................................... 32
መብት፣ ግዴታና ቅሬታ አቀራረብ ................................................................................................ 32
5.1.2 ግዴታ ....................................................................................................................... 32
5.2 የፈጻሚ አካላት መብትና ግዴታ .............................................................................. 32
5.2.1 መብት ....................................................................................................................... 32
5.3 ቅሬታ አቀራረብ ...................................................................................................... 33
ዋቢ ሰነዶች .................................................................................................................................... i
አባሪዎች ...................................................................................................................................... iii

## መግቢያ

የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ልማት በ10 ዓመት የልማት እቅድና ተከታታይ አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ላይ ተመስርቶ የራሱ የድጋፍ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶለት ላለፉት ዓመታት በኢንተርፕራይዞች ልማት አበረታች ውጤት አስገኝቷል፡፡

በዚሁ መሠረት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩ በርካታ ኢንተርፕራይዞች አስፈላጊው የአቅም ግንባታ ስልጠና፣ የፋይናንስ፣ የማምረቻና የመሸጫ ቦታ አቅርቦት እንዲሁም የገበያ ትስስር ድጋፎች እንዲያገኙ በማድረግ ገቢ ምርት በመተካት፤ በኤክስፖርት እድገት፤ በስራ እድል ፈጠራና በአጠቃላይ ለአገራዊ ምርት እድገት የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ ሆኖም የተሰጡት ድጋፎች ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በየዕድገት ደረጃቸው ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች መፍትሄ በመስጠት ረገድ ውስንነት ታይቶባቸዋል፤ እንዲሁም ለአምራች ኢንዱስትሪው መሠረቱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ልማትና መስፋፋት እንደሆነ ቀደም ሲል በተዘጋጀው የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ሰነድ ላይ በግልጽ የተቀመጠ ቢሆንም በተጨባጭ እንደታየው ለኢንተርፕራይዞቹ ሲደረግ የነበረው ድጋፍ ከአንድ የዕድገት ደረጃ ወደ ሌላ የዕድገት ደረጃ ለመሸጋገር የሚያደርጉትን ጥረት በማበረታታት ረገድ የተሟላ አፈጻጸም አልነበረውም፡፡

በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማትን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሠን የወጣው የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 526/2015 ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሰጠውን ትርጓሜ መሠረት በማድረግ ኢንተርፕራይዞችን እንደ ዕድገት ደረጃቸው በመክፈል አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት ከአንድ ደረጃ ወደሚቀጥለው እንዲሸጋገሩ ማስቻል ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህ በጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፖሊሲ ሰነድ መሠረት እያንዳንዱን የኢንተርፕራይዝ ደረጃ በንዑሳን የዕድገት ደረጃዎች እንደሚከተለው መክፈል አስፈልጓል፡፡ እነሱም ጀማሪ ደረጃ፣ ማደግ (Growth) ደረጃ እና መብቃት (Maturity) ደረጃ ናቸው፡፡

በመሆኑም ይህንን የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ መሠረት በማድረግ ኢንተርፕራይዞቹ የሚያስፈልጓቸውን ድጋፎች አሳታፊ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማቅረብ እንዲሁም ይበልጥ ለአሰራር በሚያመች መልኩ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በደንብ ቁጥር 526/2015 አንቀጽ 5(2) መሠረት ይህ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡

ማንዋሉ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የእድገት ደረጃዎች፣ የዕድገት ደረጃ ሽግግር መስፈርቶች፣ በየዕድገት ደረጃዎቹ የሚሰጡ ድጋፎች፣ የማንዋሉ ተጠቃሚዎችና ለዚህ ማንዋል ተፈጻሚነት ሚና ያላቸው አካላት ተግባርና ሃላፊነት፣ የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ስርዓት፣ የኢንተርፕራይዞችና ፈጻሚ አካላት መብት፣ ግዴታና ተጠያቂነት እንዲሁም የቅሬታ አፈታት ስርዓትን በማካተት በአምስት ክፍሎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

ይህ ክፍል በውስጡ አጭር ርዕስ፣ ትርጓሜ፣ የአሰራር ማንዋሉ አስፈላጊነት፣ የማንዋሉ ህጋዊነት፣ የማንዋሉ ዓላማ፣ የማንዋሉ መርህ፣ የማንዋሉ ተጠቃሚዎች፣ የተፈፃሚነት ወሰን፣ ከማንዋሉ የሚጠበቅ ውጤት አጠቃሎ ይዟል፡፡

## 1.1 አጭር ርዕስ

ይህ የአሠራር ማኑዋል ‹‹**የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የድጋፍ አሰጣጥና የዕድገት ደረጃ ሽግግር ማንዋል**›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 1.2 ትርጓሜ

1. **"ኢንተርፕራይዝ"** ማለት አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ማለት ነው፡፡
2. **"የኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ሽግግር"** ማለት አንድ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የራሱን ጥረት እና የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በሰው ሀይል፣ በጠቅላላ ሀብት መጠን፣ በገበያ ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ በዚህ ማንዋል የተቀመጠውን የሽግግር መስፈርት በማሟላት መሸጋገር የሚያስችል ስርዓት ነው፡፡
3. **"ጀማሪ ደረጃ"** ማለት በአነስተኛ ወይም በመካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ደረጃ በንግድ ህጉ ተመስርተው እና ሕጋዊ ሰውነት ይዘው የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ተግባር የሚጀምርበት ነው፡፡
4. **"የማደግ ደረጃ"** ማለት አንድ በአነስተኛ ወይም በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ ኢንተርፕራይዝ በራሱ ጥረት ወይም የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በጀማሪ ደረጃ ላይ ከነበረው የሰው ኃይል ቁጥርና የጠቅላላ ሀብት መጠን ዕድገት በማሳየት እና በገበያ ላይ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ ሆኖ ትርፋማነቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡
5. **"የመብቃት ደረጃ"** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ መዋቅሩን እና አሰራሩን ሙያዊ በማድረግ፣ የተለያዩ የድጋፍ ፓኬጆችን በተሳካ ሁኔታ በመጠቀም በገበያ ውስጥ በዋጋና በጥራት ብቁ ተወዳዳሪ እና ትርፋማ ሆኖ የገበያ ድርሻውን ለማሳደግ ተጨማሪ መዋዕለ ንዋይ በሥራ ላይ ካዋለ ነው፡፡
6. **"የሙያ ብቃት ማረጋገጫ"** ማለት አንድ ባለሙያ በተዘጋጀው የሙያ ደረጃ መስፈርት መሠረት የሚጠበቅበትን ብቃት መያዙ በምዘና የሚረጋገጥበት ሥርዓት ነው፡፡

7. **“የገበያ ትስስር”** ማለት ለአምራች ኢንተርፕራይዞች የገበያ እድል ለመፍጠር ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፤ በሀገር ውስጥና በውጪ ሃገር ከሚገኙ አነስተኛ፤ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ጋር በግዢና ሽያጭ በጎንዮሽና በተዋረድ በውል ስምምነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት የሚፈጠር የግብይት ሥርዓት ነው፡፡
8. “የፈፃሚ አካላት ” ማለት የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት፣ በክልል ዘርፉን የሚመሩና የሚደግፉ ቢሮዎች፣ የዞን ወይም ክፍለ ከተማ አደረጃጀቱን የሚመሩና የሚደግፉ ጽ/ቤቶች፣ የወረዳ ወይም የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ወይም ጽ/ቤቶች፣ የክህሎት እና ስልጠና ተቋማት፣ የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትን ያጠቃልላል፡፡
9. **“ዞን ወይም ክፍለ ከተማ”** ማለት ከክልል ወይም ከከተማ አስተዳደር ቀጥሎ ያለ አስተዳደራዊ መዋቅር ነው፡፡
10. **“ ደንብ ”** ማለት የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አደረጃጀት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ ደንብ ቁጥር 526/2015 ነው፡፡
11. በደንቡ አንቀጽ 2 ላይ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ማንዋል ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
12. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው ሁሉ የሴትን ጾታ ያካትታል፡፡

## 1.3 የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ማንዋል በማንኛውም አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን የዘርፉ አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት የዕድገት ደረጃ ሽግግር የድጋፍ ማዕቀፍ ለመተግበር የሚያስችል የተሟላ፣ የተቀናጀና ዘላቂነት ያለው የሽግግርና ድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓት እንዲከተሉ በማድረግ ላይ የተወሰነ ነው፡፡

## 1.4 የማንዋሉ ህጋዊነት

ማንዋሉ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አደረጃጀት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን ደንብ ቁጥር 526/2015 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.5 የማኑዋሉ ዓላማ

የዚህ አሰራር ማንዋል ዋና ዓላማ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ ለመወሰንና ለማሸጋገር፣ የዕድገት ደረጃቸውን ታሳቢ ያደረገ ወጥነትና ግልጽነት በተሞላበት አግባብ የተቀናጁና የተደራጁ ድጋፎችን በመስጠት የከፍተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት መሠረት እንዲሰፋ ማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ነው፡፡

የማንዋሉ ኢንዱስትሪዎች

## 1.6 የማኑዋሉ አስፈላጊነት

የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ ለመወሰንና ለማሸጋገር የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት የዘርፉን ልማት ቀልጣፋ፣ ብቁና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማሳደግ እና የዕድገት ደረጃን መሠረት ያደረገ የተቀናጀ ድጋፍ መስጠት የሚችል ተቋማዊ አቅም በየደረጃው መፍጠር እንደ ዋና መነሻ የተወሰደ ሲሆን ይህን ማንዋል ማዘጋጀት ያስፈለገበት ምክንያት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- እስከአሁን በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች እየተሰጡት ያሉ ድጋፎች በየደረጃቸው ለገጠሟቸው ችግሮች መፍትሔ በመስጠት ረገድ አጥጋቢ ሆኖ ባለመገኘቱ፤
- ለከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ አንዱስትሪ መሠረቱ የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች መልማትና መስፋፋት እንደሆነ በጥቃቅን እና አነስተኛ ልማት ስትራቴጂ ሰነድ (2004 ዓ.ም) ላይ በግልጽ የተቀመጠ ቢሆንም ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ለኢንተርፕራይዞቹ ሲደረግ የነበረው ድጋፍ ከአንድ የዕድገት ደረጃ ወደ ሌላ የዕድገት ደረጃ ለመሸጋገር የሚያደርጉትን ጥረት በማበረታታት ረገድ የተሟላ አፈጻጸም ያልነበረ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 526/2015፣ የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፖሊሲ (2016 ዓ.ም) እና የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሽግግር ስትራቴጂ (2016 ዓ.ም) መሠረት አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት ከአንድ ደረጃ ወደሚቀጥለው እንዲሸጋገሩ ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤
- የሽግግር ድጋፍ አሰጣጥ ወጥነት ባለው ሁኔታ በመረጃ ላይ ተደግፎ ለመወሰን የሚያስችል የአሰራር ስርአት በመዘርጋት አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ለጠቅላላ አገራዊ ኢኮኖሚ እና ስራ ዕድል ፈጠራ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱ፤
- የዕድገት ደረጃ ሽግግርና ድጋፍ አሰጣጡን አሳታፊ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ ለማድረግ እንዲሁም ለአሰራር በሚያመች መልኩ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

## 1.7 የማኑዋሉ መርሆዎች

ማኑዋሉ የተዘጋጀበትን ዓላማ ከማሳካት ጋር ተያይዞ የሚከተሉት መሰረታዊ መርሆች ይኖሩታል፡፡

- ኢንተርፕራይዞች የሚያገኟቸው ድጋፎች የዕድገት ደረጃን ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ማድረግ፤
- የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ሚና ያለው መሆኑን መረዳት፤
- የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር ግልፀኝነት፣ ተጠያቂነት እና አሳታፊ በሆነ መልኩ መተግበር፤
- የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር ዝርዝር አፈጻጸም በዚህ ማንዋል መሰረት እንዲሆን ማድረግ፣

## 1.8 የማኑዋሉ ተጠቃሚዎች

የአሰራር ማንዋሉ ተጠቃሚዎች በዋናነት አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ሲሆኑ ፍላጎትና ክፍተታቸውን መሠረት ያደረገ ለዕድገት ደረጃቸው የሚመጥን ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

በየደረጃው የሚገኙ የዘርፉ ልማት አስፈጻሚ አካላት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃቸውን መሠረት ያደረገ ድጋፍ በመስጠት የዘርፉን ልማት እንዲያሳልጡ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ስለሚያስችላቸው የዚህ አሰራር ስርዓት ተጠቃሚ ናቸው፡፡

## 1.9 የሚጠበቅ ውጤት

ይህ ማንዋል የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግርና ድጋፍ አሰጣጥ ስራዎች ሙያዊና ሳይንሳዊ እንዲሆኑ ያስችላል፤ የዘርፉ ልማት አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት መካከል የትብብር መንፈስና መተማመንን በማጎልበት ምቹ የሥራ አካባቢ ይፈጥራል፤ የተጠያቂነት፣ የግልፀኝነት እና የአሳታፊነት ስርዓት ያረጋግጣል፡፡ ማንዋሉ ተቋማዊ አቅም በመፍጠር የአስፈጻሚ አካላትን አሰራር እንደሚያሻሽል የሚጠበቅ ሲሆን በትግበራ ሂደቱም የሚከተሉትን ውጤቶች እንደሚያስገኝ ይጠበቃል፡-

1. ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ይጨምራል፣
2. ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የተሸጋገሩ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ይጨምራል፣

# ክፍል ሁለት

# የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ እና የሽግግር መስፈርቶች

## 2.1 የኢንተርፕራይዝ ዕድገት ደረጃ

የኢንተርፕራይዝ ዕድገት ደረጃዎች ከሀገር ሀገር ይለያያሉ፡፡ ለአብነት ያክል በማሌዥያ ኢንተርፕራይዞች በአራት የዕድገት ደረጃዎች ማለትም በምስረታ፣ በማደግ፣ መስፋፋት እና በመብቃት ደረጃዎች የሚያልፉ ሲሆን በጃፓን ደግሞ በሶስት የዕድገት ደረጃዎች ማለትም በምስረታ፣ ማጠናከሪያ እና በመብቃት ደረጃዎች ያልፋሉ፡፡ ከሁለቱ ሀገራት ተሞክሮ በመውሰድ በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዞች በሶስት ማለትም በምስረታ/ጀማሪ፣ በማደግ እና በመብቃት የእድገት ደረጃዎች እንዲያልፉ የሚደረግ ሲሆን ድጋፍ አሰጣጡም የዕድገት ደረጃቸውን ያገናዘበ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (ቁጥር 526/2015) ለኢንተርፕራይዝ የተቀመጠው ትርጓሜ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንተርፕራይዞች በሶስት ደረጃዎች በጀማሪ፣ በማደግ እና በመብቃት የዕድገት ደረጃዎች እንዲያልፉ የሚደረግ ሲሆን የሚሰጣቸው የድጋፍ አይነትም በማንዋሉ ክፍል ሁለት ከተራ ቁጥር 2.3.1 እስከ ተራ ቁጥር 2.3.3 በተቀመጠው መሰረት ያላቸውን የዕድገት ደረጃ ያገናዘበ ይሆናል፡፡

በንግድ ህጉ መሰረት ተመዝግበው ወደ ዘርፉ የገቡ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የፈጠሩት ቋሚ የሥራ ዕድልና ጠቅላላ የሀብት መጠን መሰረት በማድረግ በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ዓይነት ተለይተው የጀማሪ፣ ታዳጊ፣ መብቃት የዕድገት ደረጃ ይሰጣቸዋል፡፡ በማንዋሉ ክፍል ሁለት ተራ ቁጥር 2.3 ስር የተቀመጡትን የዕድገት ደረጃ መመዘኛ መስፈርቶች ኢንተርፕራይዙ አሟልቶ እስከተገኘ ድረስ እያንዳንዱን የዕድገት ደረጃ ሳይጠብቅ ወደ ሌላው የዕድገት ደረጃ ሊሸጋገር ይችላል፡፡

## 2.2 በዕድገት ደረጃ ሽግግር አገልግሎት አሰጣጥ የተግባራት ቅደም ተከተል

የዕድገት ደረጃ ሽግግር አገልግሎት ለመስጠት የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል ማከናወን ይገባል፤

2.2.1 የወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር የዘርፉ ልማት ጽህፈት ቤት የዕድገት ደረጃ ሽግግር ባለሙያዎች ወይም ለዚህ ስራ በሚቋቋም የባለሙያዎች ቡድን አማካኝነት የኢንተርፕራይዞችን መረጃ በቅጽ 01 መሠረት መሰብሰብ፣

2.2.2 በማንዋሉ ክፍል ሁለት ተራ ቁጥር 2.3 በተዘረዘረው መስፈርት መሰረት የተሰበሰበውን መረጃ በቅጽ 02 መሠረት በመሙላት የዕድገት ደረጃ ሽግግርን መወሰን፣

**2.2.3 ከጀማሪ ወደ ታዳጊ እና ከታዳጊ ወደ መብቃት የዕድገት ደረጃ የሚሸጋገሩ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች መረጃ በማደራጀት እንዲጸድቅ ለዞኑ የዘርፉ ልማት ጽ/ቤት መላክ፣**

2.2.3.1 የዞኑ ጽ/ቤት ከወረዳ/ከተማ አስተዳደር ጽህፈት ቤቶች የተላከውን መረጃ በመስፈርቱ መሰረት መላኩን የመስክ ጉብኝት በማድረግ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ፣

2.2.3.2 የመስክ ግኝት ሪፖርት በማዘጋጀት ለዞኑ /ጽ/ቤት ኃላፊ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ ማጸደቅ፣

2.2.3.3 በዞኑ ጽ/ቤት የዕድገት ደረጃ ሽግግር ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ውሳኔ በተሰጣቸው ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ልክ ሰርተፍኬት በ**ቅጽ** *05* መሰረት ማሳተም፣

2.2.3.4 የዕድገት ደረጃ ሽግግር ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ውሳኔ ለተሰጣቸው ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ሰርትፍኬት መስጠት።

**2.2.4 ከአነስተኛ ወደ መካከለኛና ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ የሚሸጋገሩ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን መረጃ በማደራጀት ለዞኑ የዘርፉ ልማት ማንዋል/ጽቤት መላክ፣**

2.2.4.1 የዞኑ ጽ/ቤት ከወረዳ/ከተማ አስተዳደረር ጽህፈት ቤቶች የተላከውን መረጃ በመስፈርቱ መሰረት መላኩን የመስክ ጉብኝት በማድረግ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ፣


2.2.4.2 የመስክ ጉብኝት ሪፖርት በማዘጋጀት እንዲጸድቅ ለክልል የዘርፉ ልማት ቢሮ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፣

2.2.4.3 በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት መስፈርቱን ያሟሉ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር ማጽደቅ፤

2.2.4.4 የዕድገት ደረጃ ሽግግር ሰርተፊኬት እንዲያገኙ በክልል ቢሮው ውሳኔ በተሰጣቸው ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ልክ ሰርተፍኬት በቅጽ 05 መሰረት ማሳተም፤

2.2.4.5 የዕውቅናና ምረቃ መርሃ-ግብር በማዘጋጀት ሽግግር ላደረጉ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በይፋ እውቅና መስጠት፤

**ስዕል 1. በዕድገት ደረጃ ሽግግር አገልግሎት አሰጣጥ የተግባራት ትስስር (Framework)**



## 2.2 የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር ዋና ዋና መስፈርቶች

የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አራት (4) ዋና ዋና መመዘኛ መስፈርቶችን መሰረት ተደርጎ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

### 1) የተፈጠረ ቋሚ የስራ ዕድል መጠን

#### 1.1) የቁልፍ ቃላት ፍቺ /operational definition/ እና የመረጃ አያያዝ

**ቋሚ የሥራ እድል** ማለት በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ የሙሉ ጊዜ ተቀጣሪ በመሆን የሰራተኞች ደሞዝ መክፈያ ሰነድ ወይም በፔይሮል ክፍያ ለሚያገኙ ዜጎች የተፈጠረ የሥራ ዕድል ማለት ነው::

ቋሚ የስራ ዕድል በሁለት አማራጮች ይፈጠራል፡፡ አንዱ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም የሚፈጠር ሲሆን ሌላው በቅጥር የሚፈጠር የስራ ዕድል ነው፡፡ ኢንተርፕራይዝ በማቋቋም የሚፈጠር የስራ ዕድል ዜጎች የንግድ ህጉን መሰረት በማድረግ በመረጡት የስራ መስክ በግል ኢንተርፕራይዝ፤ በሽርክና እና በአክሲዮን ተደራጅተው ወደ ስራ ሲገቡ የሚፈጠር የስራ ዕድልን ሲሆን በቅጥር የሚፈጠር የስራ ዕድል በአዲስ ወይም በነባር ኢንተርፕራዝ ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ተቀጥረው ለሚሰሩ ዜጎች የሚፈጠር የስራ ዕድል ነው፡፡

በዚህ መሠረት ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዙ የፈጠረው ጠቅላላ ቋሚ የስራ ዕድል የኢንተርፕራይዙን ባለቤቶች/አባላት ጨምሮ በቅጥር የተፈጠረ ቋሚ የስራ ዕድል ይሆናል፡፡ መረጃው በአባሪው ላይ በተቀመጠው ቅጽ 02 መሠረት ተሞልቶ ይያዛል፡፡

ቋሚ የስራ ዕድል መፈጠሩን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውለው ህጋዊ ሰነድ የሰራተኞች ደመወዝ መክፈያ ሰነድ (Payroll) ይሆናል፡፡

#### 1.2) የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች

##### 1.2.1) ከጀማሪ ወደ ታዳጊ ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች

(ሀ) አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ከ26 እስከ 35 ሰራተኞች ቋሚ የሥራ ዕድል የፈጠረ መሆን ይኖርበታል፡፡

(ለ) መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ከ76 እስከ 85 ሰራተኞች ቋሚ የሥራ ዕድል የፈጠረ መሆን ይኖርበታል፡፡

**1.2.2) ከታዳጊ ወደ መብቃት ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች**

(ሀ) አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ከ36 እስከ 50 ሰራተኞች ቋሚ የሥራ ዕድል የፈጠረ መሆን ይኖርበታል፡፡

(ለ) መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ከ86 እስከ 100 ሰራተኞች ቋሚ የሥራ ዕድል የፈጠረ መሆን ይኖርበታል፡፡

**1.2.3) ከአነስተኛ መብቃት ወደ መካከለኛ ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች**

(ሀ) አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የፈጠረው የሥራ ዕድል ከ50 ሰራተኞች በላይ በቋሚነት የሥራ ዕድል የፈጠረ መሆን ይኖርበታል፡፡

**1.2.4) ከመካከለኛ መብቃት ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች**

(ሀ) መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ከ100 ሰራተኞች በላይ ቋሚ የሥራ ዕድል የፈጠረ መሆን ይኖርበታል፡፡

**2) ጠቅላላ የሀብት መጠን**

**2.1 የቁልፍ ቃላት ፍቺ** /operational definition/ **እና የመረጃ አያያዝ/**

ለኢንተርፕርይዙ ገቢ ለመፍጠር የፋይናንስ ደህንነትን ለማረጋገጥ ወይም ለኢንተርፕራይዝ እሴት ለመጨመር፣ የኢንቨስትመንት ወይም የንግድ እንቅስቃሴን ለማስፋት የሚጠቅም ሀብት **ጠቅላላ ሀብት** እንለዋለን ፡፡

**ጠቅላላ ሀብት** ስንል በኢንተርፕራይዙ ስም በተከፈተ የባንክ ወይም ማይክሮ ፋይናንስ ሂሳብ ቁጥር የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ፣ ጥሬ ዕቃ፣ ማሽነሪ፣ ተሽከርካሪ፣ በመጋዘን ወይም በመሸጫ ሱቅ ላይ የሚገኙ ያለቀላቸው ወይም በከፊል ያለቀላቸው ምርቶች ወይም ማስረጃ ያላቸው ሆኖ ገንዘብ ሳይቀበል በዱቤ የተሸጡ ምርቶች ወይም ተሰብሳቢዎች፣ በኢንተርፕራይዙ ስም የሚቆጠቡ ቁጠባዎችና እቁቦች፣ ከተለያዩ ባንኮች/ማይክሮ ፋይናንሶች/ ግለሰቦች ኢንተርፕራይዙ የተበደራቸው ጥሬ ገንዘብ/ማሽነሪዎች/መገልገያ እቃዎች/ጥሬ እቃዎች፣ ለስራው ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በኢንተርፕራይዙ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች፣ የፈጠራ ባለቤትነት፣ የንግድ ምልክቶች ወይም በጎ ፈቃድ ያሉ ተጨባጭ የሆኑም ያልሆኑም የሀብት አይነቶች እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፤

በአጠቃለይ ጠቅላላ ሀብት ማለት ከፍ ብለው የተዘረዘሩትን የሀብት አይነቶች የሚያጠቃልል ሆኖ የአንድ ኢንተርፕራይዝ የተከፈለ ካፒታል እና በብድር የተገኘ ሀብት (liablity) ድምር ውጤት ሲሆን እነዚህ ጠቅላላ ሀብቶች በኢንተርፕራይዙ ስም በማስረጃ ተደግፎ መመዝገብ አለባቸው፡፡

በሒሳብ አያያዝ የሒሳቦችና የሒሳብ አርዕስቶች ግንኙነት የሚገለጽበት ቀመር የሂሳብ አያያዝ ቀመር /accounting equation/ የሚባል ሲሆን የጠቅላላ ሀብት መጠን ለማወቅ ይህንኑ የሂሳብ አያያዝ ቀመር እንጠቀማለን፡፡ ይኸውም ጠቅላላ ሀብት እኩል ይሆናል ዕዳ ሲደመር ካፒታል በመባል ይታወቃል፡፡ በሌላ በኩል ይህ ቀመር የሀብት እና ዕዳ ቀመር በመባል ይታወቃል፡፡

**ጠቅላላ ሀብት = ዕዳ + ካፒታል**

***ዕዳ ማለት***፡- ኢንተርፕራይዙ ስራውን ለመጀመርና ለማስፋፋት ከተለያዩ አበዳሪ ተቋማት፣ ግለሰቦች፣ በውል የተበደረው እና በዱቤ የገዛው እቃን ወይም አገልግሎትን በሙሉ የሚያካትት ሲሆን ከኢንተርፕራይዙ ጠቅላላ ሀብት ላይ ካፒታል ሲቀነስ ማለትም ነው፡፡

**ዕዳ = ጠቅላላ ሀብት - አንጡራ ሀብት**

**ካፒታል** ማለት፡- ከጠቅላላው የኢንተርፕራይዙ ሀብት የአበዳሪዎች ድርሻ እና ሌሎች እዳዎች ከተቀነሰ በኂላ ያለው ቀሪ ሀብት አንጡራ ሀብት ወይም ካፒታል ይባላል፡፡

**ካፒታል = ጠቅላላ ሀብት - ዕዳ**

**<u>ምሳሌ -1፡</u> (የጠቅላላ ሃብት፣ ዕዳ እና ካፒታል ማሳያ)**

አቶ አዱኛ ሉሲ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በሚል የንግድ ስያሜ 2,000,000 ብር ከራሱ፣1,000,000 ብር ከቤተሰብ በስጦታ በድምሩ በ3,000,000.00 ብር በጥሬ ገንዘብ እና በ5 ዓመት ተከፍሎ የሚያልቅ 3,000,000 ብር የተገዙ 3 የእንጨት እና ብረታ ብረት ማሽን ከኤቢሲ አክሲዮን ማህበር እና በ6 ወር ተከፍሎ የሚያልቅ የ2,100,000 ብር ጥሬ እቃ ከሀሁ አክሲዮን ማህበር በዱቤ የወሰደ ሲሆን፤ በአዲስ አበባ ከተማ ለስራው ይውላል ብሎ 13,000,000 ብር አስገንብቶ ሰኔ 29/2016 ዓ.ም ባስመረቀው የማምረቻ ህንፃ ላይ የእንጨት እና ብረታ ብረት የማምረት ስራ ሰኔ 30/2016 ዓ.ም ስራን ቢጀምር የኢንተርፕራይዙን የሀብትና ዕዳ መገለጫ /Balance Sheet/ በመስራት የጠቅላላ ሀብት፣ የዕዳ እና የካፒታል መጠኑን ለማሳየት እንደሚከተለው ቀርቧል፤

**ሉሲ ኃ/የ/የግል/ማህበር**

**የሀብትና የዕዳ መገለጫ**

**ሰኔ 30/2016 ዓ.ም**

**ሀብት**

**<u>ተንቀሳቃሽ ሀብት፡</u>**

ጥሬ ገንዘብ ………………..………3,000,000.00

የጥሬ እቃ…………………………………2,100,000.00

**የተንቀሳቃሽ ሀብት ድምር…………………………….............5,100,000.00**

**<u>ቋሚ ሀብት</u>**

የጋርመንት ማሽን ……………..……..3,000,000.00

ሕንፃ …………………..……………..….13,000,000.00

**የቋሚ ሀብት ድምር …………………………………………………16,000,000.00**

**የአጠቃላይ ሀብት ድምር ……………………………..………….. 21,100,000.00**

**ዕዳ**

አጭር ጊዜ ብድር (ሀሁ)…… ………...2,100,000.00

የረጅም ጊዜ ብድር (ኤቢሲ አ.ማ)………3,000,000.00

የጠቅላላ ዕዳ ድምር ……………………………………..…………**5,100,000.00**

**ካፒታል**

የአቶ አዱኛ መዋጮ……………………..2,000,000.00

ስጦታ……………………………………1,000,000.00

የማምረቻ ህንፃ…………………………..13,000,000.00

የካፒታል ድምር…………………………………………………………**16,000,000.00**

**የዕዳና የካፒታል ድምር ………………………………………………….21,100,000.00**

የጠቅላላ ሀብት መጠን የመረጃ ምንጭ የሚሆነው ከኢንተርፕራይዙ የሀብትና ዕዳ መገለጫ /Balance sheet/ ሆኖ መረጃው ከኦዲት ሪፖርት የሚወሰድ ይሆናል፡፡ ኦዲት ያስደረጉ ኢንተርፕራይዞች መረጃ በአባሪው ላይ በተገለጸው ቅጽ 01 ተሞልቶ ይያዛል፡፡

## 2.2) የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች

**2.2.1)** ከጀማሪ ወደ ታዳጊ ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች

(ሀ) አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የጠቅላላ ሀብት መጠኑ ከብር 2,000,001 እስከ 6,000,000 መሆን ይኖርበታል፡፡

(ለ) መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የጠቅላላ ሀብት መጠኑ ከብር 25,000,001 እስከ 55,000,000 መሆን ይኖርበታል፡፡

2.2.2) ከታዳጊ ወደ መብቃት ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች

(ሀ) አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የጠቅላላ ሀብት መጠኑ ከብር 6,000,001 እስከ 10,000,000 መሆን ይኖርበታል፡፡

(ለ) መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የጠቅላላ ሀብት መጠኑ ከብር 55,000,001 እስከ 90,000,000 መሆን ይኖርበታል፡፡

**2.2.3) ከአነስተኛ መብቃት ወደ መካከለኛ ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች**

(ሀ) አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የጠቅላላ ሀብት መጠኑ ከብር 10,000,000 በላይ መሆን ይኖርበታል ፤ሆኖም በቋሚ የሥራ ዕድል እና በጠቅላለ ሀብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሀብት ገዥ ይሆናል፡፡

**2.2.4) ከመካከለኛ መብቃት ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች**

(ሀ) መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የጠቅላላ ሀብት መጠኑ ከብር 90,000,000 በላይ መሆን ይኖርበታል፤ ሆኖም በቋሚ የሥራ ዕድል እና በጠቅላላ ሀብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሀብት ገዥ ይሆናል፡፡

## 3) ዓመታዊ የትርፍ መጠን

### 1.1 የቁልፍ ቃላት ፍቺ /operational definition/ እና የመረጃ አያያዝ

የኢንተርፕራይዞችን ዓመታዊ ትርፍ መጠን ለማስላት የገቢን እና የወጪን ምንነት ጠንቅቆ ማወቅ ይጠይቃል፤ በመሆኑም ከዚህ በታች የገቢ እና የወጪ ጽንሰ ሀሳብ ተቀምጧል፡፡

**ወጪ ማለት፡-** ኢንተርፕራይዞች የተቋቋሙበትን አገልግሎት በመስጠት ሂደት ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በዓመት ውስጥ ወይም በተወሰነ ጊዜ ላወጧቸው ወጪዎች የሚፈፀም ክፍያ ሲሆን ለሰራተኛ የሚከፈል ደሞዝ ወጪ፣ የጥሬ ዕቃ ወጪ፣ የጉልበት ሰራተኞች የሚከፈል ወጪ፣ የዕድሳት ወጪ፣ የእርጅና ተቀናሽ ወጪ፣ የመብራት/የውሃ/የስልክ ወጪ እና ሌሎች ወጪዎችን ሁሉ የሚያጠቃልል የወጪዎች ድምር የኢንተርፕራይዙ ወጪ የሚባል ሲሆን፤ በአጠቃላይ የአምራች ኢንተርፕራይዞችን ወጪ የማምረቻ ወጪ፣ አስተዳደራዊ ወጪ እና ሌሎች ወጪዎች በሚል በሶስት ከፋፍሎ ማየት ይቻላል፤ ስሌቱም እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

| |
|---|
| አጠቃላይ ወጪ = የማምረቻ ወጪ + አስተዳደሪዊ ወጪ+ ሌሎች ወጪዎች |

**የማምረቻ ወጪ፡-** ከምርት ጋር በተያየዘ በቀጥታ የሚወጡ ወጪዎችን የማምረቻ ወጪ እንላቸዋለን። ለምሳሌ የጥሬ ዕቃ ወጪ፣ ማሽነሪ ላይ ለሚሰሩ ባለሞያዎች የሚከፍል የደመወዝ ወጪ፣ የማሽነሪ ጥገና ወጪ፣ የማሽነሪ የእርጅና ተቀናሽ እና የመሳሰሉት ወጪዎች ያጠቃልላል።

**አስተዳደራዊ ወጪ፡-** ኢንተርፕራይዙ ስራውን ለማስተደዳር የሚያወጣቸውና ምርትን ለማምረት በቀጥታ የማይወጡ ነገር ግን ለኢንተርፕይዙ ስራ አሰፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን አስተዳደራዊ ወጪዎች እንላቸዋለን፤ ለምሳሌ የቢሮ ክራይ ወጪ፣ ለአስተዳደር ሰራተኞች የሚከፈል የደሞዝ ወጪ፣ የጽህፈትና የቢሮ ዕቃዎች ወጪ፣ የህግ ጉዳዮችን ለማስፈጸም የሚወጡ ወጪዎችና የመሳሰሉት ወጪዎች ያካትታል፤

**ሌሎች ወጪዎች፡-** የማምረቻ ወጪም ሆነ አስተዳደራዊ ወጪ ያልሆኑ ወጪዎችን ሌሎች ወጪዎች እንላቸዋለን። ለምሳሌ የመሸጫ እና የማከፋፋያ ወጪዎች (የማስታወቂያ፣ የኮሚሽን፣ የማሸጊያ የትራንስፖርት፣ ወዘተ) ፣ የፋይናስ ወጪ (የብድር ወለድ ወጪ፣ ሰርቪስ ቻርጅ) ፣ ጥቃቅን/ Miscellaneous/ እና ሌሎች ያልተጠበቁ ወጪዎችን ያጠቃልላል።

<u>ምሳሌ- 2፡</u> **(የወጪ ማሳያ)**

የአንድ የቢሮ እና የቢሮ ዕቃዎት አምራች ኢንተርፕራይዝ ወጪዎች የሚከተሉት ቢሆኑ ሶስቱን የወጪ አይነቶች እንደሚከተለው ማስላት ይቻላል።

**የኢንተርፕራይዙ ወጪዎች፡-**

የጥሬ ዕቃ ወጪ ድምር (ጣውላ፣ ብሎን፣ ቨርኒሽ ፣ ቀለም) = ......2,000,000

የባንክ ብድር ወለድ ወጪ …………………………………………..12,000

የሂሳብ ሰራተኛ ደመወዝ ……………………………………………..10,000

ለማሽን ጥገና እና ኤሌክትሪክሲቲ ወጪ …………………………….18.000

የሥራ አስኪያጅ ደመወዝ …………………………………………15,000

የቢሮ እና የጽህፈት መሳሪያ ወጪ ……………………………….1,000

የትራንስፖርት መጓጓዣ ወጪ ……………………………………7,000

የአናጺዎች ደመወዝ ወጪ ………………………………………80,000

የማስታወቂያ ወጪ ……………………………………………….13,000

**የማምረቻ ወጪ** = የጥሬ ዕቃ ወጪ + የአናጺዎች ደመወዝ + የማሽን ጥገና እና ኤሌክትክትሪክሲቲ ወጪ

= 2,000,000 + 80,000 + 18,000

= 2,**098,000**

**አስተዳደራዊ ወጪዎች** = የስራ አስኪያጅ ደመወዝ + የሂሳብ ሰራተኛ ደመወዝ + የቢሮ እና የጽህፈት መሳሪያ ወጪ

= 15,000 + 10,000 + 1,000

= **26, 000**

**ሌሎች ወጪዎች** = የማስታወቂያ ወጪ+ የትራንስፖርት መጓጓዣ ወጪ + የባንክ ብድር ወለድ ወጪ

= 13,000 + 7,000 + 12,000

= **32,000**

**አጠቃላይ የኢንተርፕራይዙ ወጪ =** የማምረቻ ወጪ + አስተዳደራዊ ወጪዎች + ሌሎች ወጪዎች

= 2.098,000 + 26, 000 + 32,000

= **2,156,000**

**ዓመታዊ ገቢ**

**ዓመታዊ ገቢ ማለት፡-** የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዙ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርቱን እና አገልግሎት በመሸጥ የሚያገኘው አጠቃላይ ገቢ **ዓመታዊ ገቢ** ይባላል፡፡ ይህም ብዙውን ጊዜ "ዓመታዊ ሽያጭ" ወይም "ጠቅላላ ዓመታዊ የሽያጭ ገቢ" ተብሎ ይጠራል፡፡

ዓመታዊ ገቢ = በዓመቱ የተሸጠ ዕቃ ብዛት x የመሸጫ ዋጋ

**<u>ምሳሌ 3</u>፡** (የገቢ ማሳያ)

አንድ የቢሮና የቤት ዕቃዎች አምራች ኢንተርፕራይዝ በአንድ ዓመት ውስጥ የሚከተሉትን ምርቶች አምርቶ ቢሸጥ፤ ዓመታዊ ገቢውን እንደሚከተለው ማስላት ይቻላል፡፡

ኢንተርፕራይዙ 7,000 ወንበሮች እያንዳንዱን 1,000 ብር ቢሸጥ፤ 500 ጠረጴዛዎች እያንዳንዱን 20,000 ብር ቢሸጥ

የወንበር ዓመታዊ ገቢ = በዓመቱ የተሸጠ ወንበር ብዛት x የአንዱ ወንበር የመሸጫ ዋጋ

= 7,000 x 1,000

= **7,000,000**

የጠረጴዛ ዓመታዊ ገቢ = በዓመቱ የተሸጠ ጠረጴዛ ብዛት x የአንድ ጠረጴዛ መሸጫ ዋጋ

= 500 x 20,000

= **10,000,000**

የኢንተርፕራይዙ አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ = የወንበር ዓመታዊ ገቢ + የጠረንጴዛ ዓመታዊ ገቢ

= 7,000,000 + 10,000,000

= **17,000,000**

በዚህ መሠረት ኢንተርፕራዙ ካገኘው ገቢ ላይ ያወጣቸውን የማምረቻ፣ አስተዳደራዊ እና ሌሎች ወጪዎችን ከቀነሰ በኋላ የሚገኘው ሂሳብ ትርፍ ወይም ኪሳራ ይባላል፡፡ ኢንተርፕራይዙ ካወጣው አጠቃላይ ወጪ ገቢው በልጦ ሲገኝ ትርፍ የሚባል ሲሆን ካገኘው አጠቃላይ ገቢ ወጪው በልጦ ሲገኝ ደግሞ ኪሳራ ይባላል፡፡ ይህንንም ለማሳየት የምንጠቀምበት የሂሳብ መግለጫ/Finacial Statement የትርፍና ኪሳራ መገለጫ/Income Statement ይባላል፡፡ ኢንተርፕራይዞች በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚያገኙትን ትርፍ መልሰው ኢንቨስት ሊያደርጉት፣ ሊቆጥቡት ወይም የኢንተርፕራይዙ ባለቤቶች/አባላት በድርሻቸው ልክ ሊከፋፈሉት ይችላሉ፡፡

<u>**ምሳሌ 4**</u>**፡** (የትርፍ ማሳያ)

ሉሲ ኃ/የተ/የግል ማህበር ከሀምሌ 01/2016 ዓ.ም አስከ ሰኔ 30/2017 ዓ.ም ከዚህ በታች የተጠቀሱት ሂሳቦች አሉት፤ ስለዚህ ለኢንተርፕራይዙ የሚከተሉትን መረጃዎች በመጠቀም የትርፍና ኪሳራ መግለጫ /Income Statement/ በማዘጋጀት ዓመታዊ ትርፍ/ኪሳራን ማስላት ይቻላል፡፡

የኢንተርፕራይዙ ሂሳቦች፡-

- የብረት በር ሽያጭ…………………6,000,000
- የእንጨት በር ሽያጭ………………3,000.000
- የመሳሪያዎች የእርጅና ቅናሽ………100,000.00/300,000
- የስልክ ወጪ……………………….4,000.00
- ብረት መስኮት ሽያጭ……………..2,000,000,00
- የእንጨት መስኮት ሽያጭ…………1,500,000
- የማስታወቂያ ወጪ………………...200,000.00
- ጥሬ እቃ ወጪ……………………..5,000,000.00
- የአምራቾች/ቴክኒካል ደመወዝ……….400,000.00
- የኤሌክትሪክ ወጪ…………………..50,400.00
- የሽያጭ ሰራተኛ ደመወዝ…………...70,000.00
- የኮሚሽን  ወጪ…………………….130,000.00
- የውሃ ወጪ…………………………10,000.00

**ሉሲ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**

**የትርፍና ኪሳራ መገለጫ**

**ሰኔ 30/2017 ዓ.ም**

**ገቢ**

የብረት በር ሽያጭ……..,..6,000,000.00

የእንጨት በር ሽያጭ……..3,000,000.00

ብረት መስኮት ሽያጭ…....2,000.000,00

የእንጨት መስኮት ሽያጭ…1,500,000.00

**ጠቅላላ ሽያጭ ድምር……………………………......................…12.500,000.00**

**የማምረቻ ወጪ**

ጥሬ እቃ ወጪ………………….5,000,000.00

የአምራቾች ደመወዝ……………..400,000.00

የኤሌክትሪክ ወጪ…...……………50,400.00

የመሳሪያዎች የእርጅና ቅናሽ…..…300,000.00

**የማምረቻ ወጪ ድምር………………………………...............…...…5,750,400**

**የማምረቻ ትርፍ…………………………………………………………6,749,600**

**የአስተዳደርዊ እና የሽያጭ ወጪ**

የሽያጭ ሰራተኛ ደመወዝ……...70,000.00

የውሃ ወጪ……………………10,000.00

የስልክ ወጪ……………….….…4,000.00

የማስታወቂያ ወጪ……………200,000.00

የኮሚሽን ወጪ………………130,000.00

ድምር………………………………………… **414,000.00**

ትርፍ ከታክስ በፊት…………………………………………………….**6,335,600**

ትርፍ ግብር 30%…………………………………………….………..1,900,,680

**የተጣራ ትርፍ…………………………………………………………..…4,434,920**

የትርፋማነት የመረጃ ምንጭ የሚሆነው የኢንተርፕራይዙ የትርፍና ኪሳራ መገለጫ/Income Statment/ ሆኖ መረጃው ከኦዲት ሪፖርት የሚወሰድ ይሆናል፡፡ ኦዲት ያስደረጉ ኢንተርፕራይዞች መረጃ በአባሪው ላይ በተገለጸው ቅጽ 01 ተሞልቶ ይያዛል፡፡

### 3.2) የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች

#### 3.2.1) ከጀማሪ ወደ ታዳጊ ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች

(ሀ) አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ በዓመቱ ካደረገው ሽያጭ የተጣራ ትርፍ መጠኑ ቢያንስ 11% መሆን ይኖርበታል፡፡

(ለ) መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ በዓመቱ ካደረገው ሽያጭ የተጣራ ትርፍ መጠኑ ቢያንስ 14% መሆን ይኖርበታል፡፡

#### 3.2.2) ከታዳጊ ወደ መብቃት ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች

(ሀ) አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ በዓመቱ ካደረገው ሽያጭ የተጣራ ትርፍ መጠኑ ቢያንስ 12% መሆን ይኖርበታል፡፡

(ለ) መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ በዓመቱ ካደረገው ሽያጭ የተጣራ ትርፍ መጠኑ ቢያንስ 15% መሆን ይኖርበታል፡፡

## 4) ወቅታዊ የማምረት አቅም አጠቃቀም

በዚህ ዋና መስፈርት ስር የሚገኙ ንዑሳን መስፈርቶችን (የማምረት አቅም አጠቃቀም፣ የተኪ ምርት መጠን ዓመታዊ ዕድገት እና የወጪ ምርት ገቢ ዓመታዊ ዕድገት) ለማብራራት የቃላት ፍቺዎች፣ ቀመሮችና ምሳሌዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 4.1) የማምረት አቅም አጠቃቀም ልኬት

#### 4.1.1) የቁልፍ ቃላት ፍቺ /operational definition/ እና የመረጃ አያያዝ

**የአቅም አጠቃቀም** ማለት አንድ ድርጅት ያሉትን የተለያዩ ግብአቶች በምን ያህል የብቃት ደረጃ ተጠቅሞ የታለመለትን ምርት ወይም ውጤት አሳክቷል የሚለውን የምንለካበት ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካች ሲሆን ልኬቱም በመቶኛ የሚገለጽ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የማምረት አቅም አጠቃቀም አንድ ተቋም ሙሉ የማምረት አቅሙ ላይ መድረስ ስለመቻሉ እና አለመቻሉ የሚገመገምበትና የሚታወቅበት አንዱ የውጤታማነት መለኪያ ዘዴ ነው፡፡

የአቅም አጠቃቀምን ለመለካት ሁለት መሰረታዊ ስልቶች/ዘዴዎች ያሉ ሲሆን፣ እነሱም፡- በመረጃ ላይ የተመሰረቱ የመለኪያ ዘዴዎች (Data-Based Methods) እና በዳሰሳ ጥናት ላይ የተመሰረቱ ዘዴዎች (Survey-Based Methods) በመባል ይታወቃሉ፡፡ በመረጃ ላይ የተመሰረቱ የመለኪያ ዘዴዎች በቀጥታ ከአምራቾች መረጃ ከማሰበሳብ ይልቅ በአገር አቀፍ የስታስቲካል መረጃዎች ላይ በመመስረት የአቅም አጠቃቀምን ለመለካት ይሞክራል፡፡ ሌላው የአቅም አጠቃቀምን ለመለካት ሥራ ላይ የሚውለው ዘዴ ኢንተርፕራይዞችን አቅማቸው ምን ደረጃ ላይ እንደሆነ በመጠየቅ የሚያሰላ ዘዴ

ነው፡፡ የዳሰሳ ጥናት ዘዴ ከአቅም ጋር የተያያዙ ቀጥተኛ ጥያቄዎችን በማንሳት በሚሰጡ መልሶች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ አካሄድ በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ዘዴዎችን በመጠቀም ማግኘት የማይቻሉ የመረጃ ዓይነቶችን ማግኘት ይቻላል፡፡

የማምረት አቅም አጠቃቀም ከዚህ በታች በተቀመጠው ቀመር መሠረት የሚለካ ይሆናል፡፡

የማምረት አቅም አጠቃቀም (በመቶኛ) = (አሁናዊ የማምረት አቅም/ሊደረስበት የሚችል የማምረት አቅም)*100

Capacity Utilization (%) = (Actual Capacity/Attainable Capacity)*100

- **ምናባዊ/ሀሳባዊ የማምረት አቅም** (Design or Installed Capacity) **ማለት** የማምረት አቅም አጠቃቀምን ሊያሳንሱ የሚችሉ ሁነቶችን ከግምት አያስገባም፡፡ የማምረት አቅም አጠቃቀም በምንም ምክንያት ሳይቀንስ በሃሳባዊ የሚሰራ ስሌት በመሆኑ ትክክለኛውን የአቅም አጠቃቀም አሃዝ ለማግኘት አያስችልም፡፡ ይህ የማምረት አቅም አንድ ድርጅት ያሉትን ግብአቶች (resources) ሙሉ በሙሉ መጠቀም ሲችል የሚደርስበትን የአቅም አጠቃቀም ደረጃ ያሳየናል፤ ሆኖም ግን አንድ ድርጅት በምናባዊ የማምረት አቅሙ ልክ ምርት ሊያመርት የሚችልበት ሁኔታ ብዙም አያጋጥምም፡፡
- **ሊደረስበት የሚችል የማምረት አቅም**/Attainable Capacity/ **ማለት** ምናባዊ በሆነው የማምረት አቅም አጠቃቀማችን ልክ እንዳናመርት እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮችን በተወሰነ መልኩ ታሳቢ ያደርጋል፡፡ ከምናባዊ የማምረት አቅም ጋር ሲነጻጸርም ዝቅ ያለ ሆኖ ይገኛል፤ የማምረት አቅም አጠቃቀም የሚለካው ሊደረስበት ከሚችለው የማምረት አቅም ጋር በማነጻጸር መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡
- **የተደረሰበት/አሁናዊ የማምረት አቅም**/Actual or Existing Capacity/ **ማለት** በትክክል ኢንተርፕራይዙ እያመረተ የሚገኘውን የምርት መጠን የሚገልጽ ሲሆን ተመዝግበው ከሚያዙ የምርት መጠን መረጃዎች የሚገኝ ነው፤

የኢንተርፕራይዞችን የማምረት አቅም አጠቃቀም ለመለካት ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በ2014 ዓ/ም ያዘጋጀውን እና እየተገበረው ያለውን ***‹የማምረት አቅም አመላካቶችና የአለካክ ስልቶች ማንዋል›*** መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ የኢንተርፕራይዞችን የማምረት አቅም አጠቃቀም በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አማካኝነት በመጠይቅ በተደገፈ የዳሰሳ ጥናት የሚሰበሰብ መረጃን መሠረት በማድረግ የሚለካ ይሆናል፡፡

**ምሳሌ 5፡** (የማምረት አቅም አጠቃቀም ማሳያ-1)

አንድ የፕላስቲክ ፌስታል አምራች ኢንተርፕራይዝ 3 ብሎዊንግ (ጣቃ መስሪያ) 70 ኪ.ግ በሰዓት ሊያመርቱ የሚችሉ *(ስሪት ያላቸው)* ማሽኖች እና 1 ፌስታል መስሪያ 55 ኪ.ግ በሰዓት ሊያመርት የሚችል *(ስሪት ያለው)* ማሽን ቢኖሩት ኢንተርፕራይዙ በቀን 8 የስራ ሰዓት ቢሰራ እና ከእዚህ ውስጥ 1 ሰዓት ማሽን ለማሞቅ፣ 30 ደቂቃ ማሽን ለማስተካከል (adjustment)፣ 30 ደቂቃ ደግሞ ሊወገዱ በሚችሉ የተለያዩ ምክኒያቶች ከቀኑ የስራ ሰዓት ላይ ተቀናሽ ቢሆን እና በአሁኑ ወቅት በቀን በአማካይ 270 ኪ.ግ ፌስታል የሚያመርት ቢሆን፡-

**ሀ/ የኢንተርፕራይዙ ሀሳባዊ/ምናባዊ የማምረት አቅም በቀን (Designed capacity) ስንት ይሆናል?**

- ***ሀሳባዊ/ምናባዊ የማምረት አቅም*** *የምንለው አንድ ድርጅት ያሉትን ግብአቶች (resources)* **ሙሉ በሙሉ መጠቀም ሲችል የሚደርስበትን የአቅም አጠቃቀም ደረጃ ነው፡፡ በምሳሌው የተጠቀሰው ኢንተርፕራይዝ ምናባዊ የማምረት አቅሙ በሰዓት 55 ኪ.ግ በመሆኑ ይህን ድርጅቱ በቀን ስራ ላይ በሚያውለው ሰዓት (8 ሰዓት) በማባዛት የሚገኝ ይሆናል፡፡**

በዚህ መሠረት የኢንተርፕራዙ ሀሳባዊ/ምናባዊ የማምረት አቅም (Designed capacity) በቀን

**55 ኪ.ግ*8 ሰዓት= 440 ኪ.ግ ይሆናል፡፡**

**ለ/ ኢንተርፕራይዙ ሊደረስበት የሚችል የማምረት አቅም በቀን (Attainable capacity) ስንት ይሆናል?**

- ***ሊደረስበት የሚችል የማምረት አቅም*** *የምንለው* **ምናባዊ በሆነው የማምረት አቅም አጠቃቀማችን ልክ እንዳናመርት እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮችን በተወሰነ መልኩ ታሳቢ የሚያደርግ ሲሆን ከምናባዊ የማምረት አቅም ጋር ሲነጻጸርም ዝቅ ያለ ነው፡፡ በምሳሌው የተጠቀሰው ኢንተርፕራይዝ ሊደረስበት የሚችል የማምረት አቅሙ ከምናባዊ የማምረት አቅሙ ላይ ሊወገዱ የማይችሉ (ልናስቀራቸው የማንችላቸውን) ስራዎች በመቀነስ የምናገኘው ይሆናል፤**

በዚህ መሠረት ማሽን ማሞቅ እና ማሽን ማስተካከል ሊወገዱ የማይችሉ ስራዎች በመሆናቸው እነዚህን ተግባራት ለማከናወን የሚወስደውን ጊዜ (ለማሞቅ 1 ሰዓት + ለማስተካከል 30 ደቂቃ በድምሩ 1፡30 ሰዓት በቀን) ምርትን ለማምረት ከተያዘው ሰዓት በመቀነስ (8 -1.5 = 6.5) ሊደረስበት የሚችለውን የማምረት አቅም ማስላት ይቻላል፡፡

በዚህ መሠረት ማሽኑ በ8 ሰዓት 440 ኪ.ግ የሚያመርት ከሆነ በ6.5 ሰዓት ምን ያህል ይመርታል ብለን ማስላት እንችላለን፡፡ ስለዚህ የኢንተርፕራይዙ ሊደረስበት የሚችል የማምረት አቅሙ፡-

(6.5 ሰዓት*440 ኪ.ግ)/8 ሠዓት = 357.5 ኪ.ግ ይሆናል፡፡

**ሐ/ በኢንተርፕራይዙ በቀን በአማካይ የተመረተ ምርት መጠን (Actual capacity) ስንት ነው?**

- **የተደረሰበት/አሁናዊ የማምረት አቅም** በትክክል ፋብሪካው እያመረተ የሚገኘውን የምርት መጠን የሚገልጽ ነው፡፡ በምሳሌው የተጠቀሰው ኢንተርፕራይዝ በቀን እያመረተ ያለው የምርት መጠን 270 ኪ.ግ በመሆኑ፡-

አሁናዊ የማምረት አቅሙ (Actual capacity) = 270 ኪ.ግ ነው፡፡

**መ/ የኢንተርፕራይዙ የማምረት አቅም አጠቃቀም (Capacity utilization rate) ስንት ይሆናል?**

የኢንተርፕራይዙ የማምረት አቅም አጠቃቀም (በ%) = (አሁናዊ የማምረት አቅም/ሊደረስበት የሚችል የማምረት አቅም)*100

= (270 ኪ.ግ/357.5 ኪ.ግ)*100

= <u>75.5%</u>

**<u>ምሳሌ 6</u>**: (የማምረት አቅም አጠቃቀም ማሳያ-2)

ዱቄት፣ ፓስታና መኮሮኒ ምርቶችን የሚያመርት አንድ ኢንተርፕራይዝ ምናባዊ፣ ሊደረስበት የሚችልና አሁናዊ የማምረት አቅም አጠቃቀሙ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተገልጿል፡፡

| የምርት አይነት | ምናባዊ የማምረት አቅም (የወር) | ሊደረሰበት የሚችል የማምረት አቅም | አሁናዊ የማምረት አቅም |
|---|---|---|---|
| ዱቄት | 910,000 ኪ.ግ | 520,000 ኪ.ግ | 312,000 ኪ.ግ |
| ፓስታ | 2,600 ቶን | 2,522 ቶን | 2,080 ቶን |
| መኮረኒ | 25,000 ቶን | 17,000 ቶን | 8,600 ቶን |

- መጀመሪያ ኢንተርፕራይዙ በእያንዳንዱ ምርት ላይ ያለውን የማምረት አቅም አጠቃቀም ማስላት፣

**የማምረት አቅም አጠቃቀም (በመቶኛ) = (አሁናዊ የማምረት አቅም/ሊደረስበት የሚችል የማምረት አቅም)*100**

**መኮረኒ**
**8,600/17,000*100 = <u>51%</u>**

**ፓስታ**
**2080/2522*100 = <u>82%</u>**

**ዱቄት**
**312000/520000*100 = <u>60%</u>**

የኢንተርፕራይዙ አማካይ የማምረት አቅም አጠቃቀሙ (Capacity Utilization)

(51% + 82% + 60%)/3 = <u>64%</u>

### 4.1.2 የተኪ ምርት መጠን ዓመታዊ ዕድገት

**ተኪ ምርት ማለት፡-** ከውጭ አገር የሚገቡ ምርቶችን በዋጋ፣ በመጠን፣ በዓይነትና በጥራት ለመተካት በአገር ውስጥ የተመረተ ምርት ማለት ነው፡፡

**<u>ምሳሌ 7</u>:** (የተኪ ምርት መጠን ዓመታዊ ዕድገት ማሳያ)

አንድ የስንዴ ዱቄት ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ በ2016 ዓ.ም 37,320 ኩንታል ስንዴ ዱቄት ቢያመርት፣ በ2017 ዓ.ም 40,000 ኩንታል ስንዴ ዱቄት ቢያመርት፤ የኢንተርፕራይዙ የተኪ ምርት መጠን ዓመታዊ ዕድገት ስንት ነው?

**ዓመታዊ ዕድገት** = (40,000.00 - 37,320.00)/ 37,320.00 *100

= <u>7.2%</u>

### 4.1.3 የወጪ ምርት ገቢ መጠን ዓመታዊ ዕድገት

**የወጪ ምርት ማለት፡-** የውጭ አገር የገበያ መዳረሻን የምርት ደረጃ ባሟላ ሁኔታ በአገር ውስጥ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ተመርቶ ወደ ውጭ አገር የተላከ ሲሆን ወደ ውጭ ለመሄድ በተዘጋጁ ማጓጓዣወች ላይ ምርቶችን መጫንን ይጨምራል፡፡ (አዋጅ ቁጥር 768/2004 የወጭ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት)

**<u>ምሳሌ 8</u>:** (የወጪ ምርት ገቢ ዓመታዊ ዕድገት ማሳያ)

አንድ እንጀራ አምራች ኢንተርፕራይዝ ወደ ሰሜን አሜሪካ እና የተባበሩት አረብ ኤሚሬትስ ምርቱን በመላክ በ2016 ዓ.ም 3,000,000.00 ዶላር እንዲሁም በ2017 ዓ.ም 3,080.430.00 ዶላር ገቢ ቢያገኝ፤ የኢንተርፕራይዙ የወጪ ምርት ገቢ ዓመታዊ ዕድገት ስንት ነው?

**ዓመታዊ ዕድገት** = (3,080.430.00 - 3,000,000.00)/ 3,000,000.00*100

= <u>2.7%</u>

## 4.2) የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች

### 4.2.1) ከጀማሪ ወደ ታዳጊ ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች

(ሀ) የማምረት አቅም አጠቃቀም 55% እና ከዚያ በላይ የሆነ፣

(ለ) ለሚያመርታቸው ምርቶችና ለሚያቀርባቸው አገልግሎቶች ዘመናዊ የሥራ አመራርን የተከተለ የጥራት ሰርተፍኬት ያቀረበ እና የንግድ ሥራ ዕቅድ ያለው መሆን አለበት፣

(ሐ) የኢንተርፕራይዙ የተኪ ምርት መጠን ዓመታዊ ዕድገት ቢያንስ 4% መድረስ ይኖርበታል፣

(መ) የኢንተርፕራይዙ የወጪ ምርት ገቢ ዓመታዊ ዕድገት ቢያንስ 1% መድረስ ይኖርበታል፣

(ሠ) ከኢንተርፕራይዙ የቴክኒክ ሰራተኞች ወይም ባለሙያዎች መካከል ቢያንስ 40% የሆኑት የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኙ መሆን አለባቸው።

### 4.2.2) ከታዳጊ ወደ መብቃት ደረጃ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች

(ሀ) የማምረት አቅም አጠቃቀሙ 65% እና ከዚያ በላይ የሆነ፤

(ለ) ለሚያመርታቸው ምርቶችና ለሚያቀርባቸው አገልግሎቶች ዘመናዊ የሥራ አመራርን የተከተለ የጥራት ምስክር ወረቀት ያቀረበ እና የንግድ ሥራ ዕቅድ ያለው መሆን አለበት፣

(ሐ) የኢንተርፕራይዙ የተኪ ምርት መጠን ዓመታዊ ዕድገት ቢያንስ 6% መድረስ ይኖርበታል፣

(መ) የኢንተርፕራይዙ የወጪ ምርት ገቢ ዓመታዊ ዕድገት ቢያንስ 3% መድረስ ይኖርበታል፣

(ሠ) ከኢንተርፕራይዙ የቴክኒክ ሰራተኞች ወይም ባለሙያዎች መካከል ቢያንስ 50% የሆኑት የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኙ መሆን አለባቸው።

## 2.3 ለኢንተርፕራይዞች በየዕደገት ደረጃቸው የሚሰጡ የድጋፍ ማዕቀፎች

ኢንተርፕራይዞች ለሽግግር የሚያበቃቸው ዋናው ጉዳይ በጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፖሊሲ፣ በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማት ፍኖተ ካርታ እና በአነሰተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ሀገራዊ የሽግግር ስትራቴጂ የተመለከቱ ድጋፎችን ለመተግበር በሚወጡ የድጋፍ ማዕቀፎች መሰረት በዕድገት ደረጃቸው ማግኘት የሚገባቸውን ድጋፎች በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ ሲያገኙ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ኢንተርፕራይዞች በየዕድገት ደረጃቸው ሊያገኟቸው የሚችሉ የድጋፍ ዓይነቶች ጠቅለል ባለ መልኩ ለማስቀመጥ ተሞክሯል።

### 2.3.1 በጀማሪ ደረጃ የሚሰጥ ድጋፍ

(ሀ) ሕጋዊ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ማድረግ፣

(ለ) ከፋይናንስ ተቋማት የስራ ማስኬጃና የካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት እንዲያገኙ ማመቻቸት፣

(ሐ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣

(መ) ወቅቱን የጠበቀ የንግድ ልማት አገልግሎት አቅራቢዎችና አማካሪዎች መረጃ ተደራሽ ማድረግ፣

### 2.3.2 በማደግ ደረጃ የሚሰጥ ድጋፍ

(ሀ) ከፋይናንስ ተቋማት የስራ ማስኬጃና የካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት እንዲያገኙ ማመቻቸት፣

(ለ) ለተበዳሪነት የሚያበቃ የንግድ ሥራ ዕቅድ ዝግጅት፣ የአዋጪነት ጥናት እንዲያደርጉ መደገፍ፣ የቢዝነስ ፕላን መሰረት ያደረገ የስራ ማስፋፊያ ፋይናንስ አቅርቦት ማመቻቸት፣ የወሰዱትንም ብድር በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲያውሉ ማድረግ፣

(ሐ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣

(መ) የክልል፣ የሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ገበያ እንዲጠቀሙ ማድረግ፤ የገበያ ትስስርና የገበያ አቅምን ማሳደጊያ ድጋፍ መስጠት፣

(ሠ) የማምረቻና የመሸጫ ቦታ (ማዕከላት) በተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያ እንዲያገኙ የማመቻቸትና በተናጠል ሊያሟሏቸው የማይችሉ የጋራ መገልገያ መሳሪያዎችን እንዲሟሉ ድጋፍ ማድረግ፤

(ረ) የንግድ ልማት አገልግሎት አቅራቢዎችና አማካሪዎች መረጃ በየጊዜው ተደራሽ ማድረግ፣

### 2.3.3 በመብቃት ደረጃ ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጡ ድጋፎች

ሀ) ገበያን ለማስፋት የሚያስችል ድጋፍ፣ በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ (ISO የጥራት ስራ አመራር ስርዓት) ተጠቃሚ ማድረግ፤

ለ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት መስጠት፣

ሐ) ከፋይናንስ ተቋማት የስራ ማስኬጃና የካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት እንዲያገኙ ማመቻቸት፣

መ) የግል የንግድ ልማት አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር ትስስር በመፍጠር የዕውቀትና የክህሎት ሽግግር እንዲያገኙ ማድረግ፣

2.3.4 ከተራ ቁጥር 2.3.1 እስከ ተራ ቁጥር 2.3.3 የተጠቀሱት ዋና ዋና የድጋፍ ዓይነቶች በተሟላ ሁኔታ ተፈጻሚ ለማድረግ በሚዘጋጁ የዘርፉ የድጋፍ ማዕቀፎች መሰረት እንደ የዕድገት ደረጃቸው በዝርዝር ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል።

# ክፍል ሦስት

# የፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## 3.1 የፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

የዚህ ማንዋል አስፈላጊነት የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማቱን ቀልጣፋ፣ ብቁና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማሳደግ የዕድገት ደረጃን መሠረት ያደረገ የተቀናጀ ድጋፍ መስጠት የሚችል ተቋማዊ አቅም በየደረጃው መፍጠር ነው። በዚህ መሠረት የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ሽግግር እና ድጋፍ አፈጻጸም ማንዋል ተግባራዊነት ላይ ቀጥተኛ ሚና ያላቸው ዋና ዋና አካላት ተግባርና ኃላፊነት እንደሚከተለው ቀርቧል።

1) **ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር**

ሀ) በአነስተኛ፣ መካከለኛና በከፍተኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠርና ስኬታማ ሽግግሮች እንዲከናወኑ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣

ለ) የኢንተርፕራይዝ ሽግግር ደረጃ መሠረት ያደረጉ ድጋፎችን ውጤታማነት ይገመግማል፤ የመፍትሄ አቅጣጫዎችንም ያስቀምጣል፤

ሐ) ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞችን ይደግፋል።

2) **የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት**

(ሀ) የኢንተርፕራይዝ ልማትንና ሽግግርን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ፕሮግራምና ፕሮጀክቶች እንዲወጡ ሐሳብ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያቀርባል፣ ተዘጋጅቶ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

(ለ) ኢንተርፕራይዞችን እንደ የዕድገት ደረጃቸው የድጋፍ ማዕቀፎች አፈፃፀም መከታተልና በሂደትም ማሻሻል ስለ አተገባበራቸውም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

(ሐ) የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ የተመለከቱ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ማጠናቀርና ማሰራጨት፤

(መ) በየደረጃው ለሚገኙ የክልል እና ከተማ አስተዳደር አመራሮችና ፈጻሚዎች የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግርና ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል ላይ የአሰልጣኞች ስልጠና ይሰጣል፤

(ሠ) በሽግግር ሥራ ላይ አላሰራ ያሉ ማነቆዎችን በጥናት በመለየት የአሰራር ስርዓት እንዲሻሻል ያደርጋል፤

(ረ) የተመረጡ የላቀ አፈጻጸም ያላቸውን ወደ ከፍተኛ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች በፌደራል ደረጃ ዕውቅና እና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

(ሸ) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞችን ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር በመረከብ ድጋፍ ያደርጋል፣

3) **የክልል ዘርፉን የሚመሩና የሚደግፉ ቢሮዎች**

(ሀ) ይህን ማንዋል መነሻ በማድረግ ዝርዝር የማስፈጸሚያ የአሰራር ስርዓት ማዘጋጀት፤ ተግባራዊነቱን መከታተል፣

(ለ) በዘርፉ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች እንደ ዕድገት ደረጃቸው መንግስታዊ ድጋፎች እንዲያገኙ በማድረግ የሽግግር ስራውን የተሳለጠ ያደርጋሉ፣

(ሐ) የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግርና ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል ላይ በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮች፣ ፈጻሚዎች እና ለኢንተርፕራይዞች ግንዛቤ ማስጨበጥ፣

(መ) የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ አፈፃፀም መከታተልና መደገፍ

(ሠ) የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ለመወሰን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማሰባሰብና ማደራጀት፣

(ረ) በዚህ ማንዋል መሠረት የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ ሽግግር መወሰን፣

(ሰ) ለኢንተርፕራይዞች የሚሰጡ መንግስታዊ ድጋፎች የዕድገት ደረጃቸውን መሰረት በማድረግ እየተፈፀሙ መሆናቸውን መከታተልና ድጋፍ ማድረግ፣

(ሸ) ከአነስተኛ ደረጃ ወደ መካከለኛ ደረጃ እና ከመካከለኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ለሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ እውቅና የምስክር ወረቀት መስጠት፣

(ቀ) እስከ ታችኛው የአደረጃጀት መዋቅር ድረስ (የዞን፣ ወረዳ ፣የከተማ እና ቀበሌ) የመደገፍ፣ የማብቃት እና የክትትል ስራ ያከናውናል፤

(በ) ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልጋቸውን የመስሪያ ቦታ /መሬት/ ከሦስተኛ ወገን ይዞታ ነፃ እንዲሆን ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፣ የቦታ ካርታና ፕላን በማሠራትም እስከ መዳረሻቸው የሚዘልቅ መሠረተ-ልማት እንዲሟላላቸው ያደርጋል፤

(ተ) ለማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንደ ዕድገት ደረጃቸው በክላስተር ማዕከላት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መስፈርቶች ያዘጋጀል፤ ተፈጻሚ እዲሆን ያደርጋል፣

4) **የዞን የዞን ወይም ክፍለ ከተማ ዘርፉን የሚመሩና የሚደግፉ ጽ/ቤቶች**

(ሀ) የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ማንዋል ላይ በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮችና ፈጻሚዎች እና ለኢንተርፕራይዞች ግንዛቤ ማስጨበጥ፣

(ለ) የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ አፈፃፀም መከታተልና በወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ለሚገኘው መዋቅር ድጋፍ ያደርጋል፣

(ሐ) የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ለመወሰን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማሰባሰብና ማደራጀት፣

(መ) በአነስተኛ ደረጃ ላሉ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

5) **ከተማ ወይም የወረዳ ወይም አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች (ጽ/ቤቶች)**

(ሀ) የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ከመረጃ፣ ከሥልጠና እና ምክር አገልግሎት፣ ከግብዓት አቅርቦት፣ ከኢንተርፕርነርሽፕ እና ንግድ ልማት፣ ከሂሳብ አያያዝ፣ ከቴክኖሎጂና ማምረቻ መሣሪያ አኳያ ያሉባቸውን መሠረታዊ ችግሮች በየጊዜው እየተከታተለ በዝርዝር ይለያሉ፣

ለ) በተለዩት ችግሮች መሠረት ለኢንተርፕራይዞች እንደየዕድገት ደረጃቸው ድጋፎችን ይሰጣሉ ወይም እንዲያገኙ ያመቻቻሉ፤

(ሐ) የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ለመወሰን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ያሰባስባሉ፤ ያደራጃሉ፣

6) **የክህሎት እና ሥልጠና ተቋማት**

(ሀ) ለኢንተርፕራይዞች እንደ የዕድገት ደረጃቸው ክፍተታቸውን በመለየት የክህሎት ስልጠናና ቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር አገልግሎት ይሰጣል፣

(ለ) ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ በመለየት እና በማፅደቅ ሂደት ይሳተፋል፣

ሐ) አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ያሉባቸውን የኢንተርፕርነርሽፕ፣ የሂሳብ አያያዝ፣ የፋይናንስ፣ የገበያ ችግሮች ለማቃለል እንደዕድገት ደረጃቸው የምክርና ስልጠና አገልግሎት ድጋፍ ይሰጣሉ፣

7) **የፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት**

(ሀ) ለኢንተርፕራይዞች እንደ የዕድገት ደረጃቸው የፋይናንስ አቅርቦት ድጋፍ ያደርጋሉ፣

(ለ) ኢንተርፕራይዞችን እንደ የዕድገት ደረጃቸው በመለየት እና በመረጣ ሂደት የብድርና የቁጠባ አፈፃፀም መረጃ ያሰባስባሉ፣ ያደራጃሉ፣ ይህንንም ለሚያስፈፀመው አካል ይሰጣሉ፣

8) **የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት**

ሀ) በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ለሚገነቡ የመሥሪያ ቦታዎች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ያቀርባል፣

ለ) ለኢንተርፕራይዞች የመሥሪያ ቦታዎች የኤሌክትሪክ አቅርቦትን የሚያመቻችና ሥራውን በባለቤትነት የሚመራ የሥራ ክፍል በቡድን/ በዩኒት/ በፈፃሚ ባለሙያ ደረጃ እንዲመደብ ያደርጋል፣

ሐ) ኢኮኖሚው ላይ ያላቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ የሆኑ ምርቶችን የሚያመርቱ ኢንተርፕራይዞች እና በሁለቱ ተቋማት በጋራ በሚወጡ መመዘኛዎች መሰረት ለሚለዩ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ልዩ ክትትል ያደርጋል፣

መ) የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ተጠቃሚ የሆኑ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

9) **የስራና ክህሎት ሚኒስቴር**

ሀ) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ የተሸጋገሩ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ፕሮፋይል በማደራጀት ለኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ይልካል፣

ለ) በየክልሉ ያሉ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት እንዲጠናከሩና ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንደየዕድገት ደረጃቸው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፣

ሐ) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት መምህራንና አመራሮች ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ችግር ፈቺ ድጋፍ መስጠት እንዲችሉ የክህሎት ክፍተታቸው እየታየ በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት በኩል የአቅም ግንባታ ሥልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፣

መ) የኢንዱስትሪ ሠላም ለማስጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፤

10) **የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር**

ሀ) ከተሞች ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች መሥሪያ ቦታ የለማ ቦታ እንዲዘጋጅና በማስተር ፕላናቸው እንዲያካትቱ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

ለ) ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች መሥሪያ ቦታ መገንቢያ የሚውሉ መሬቶችን ይለያል፤ የተለዩትን መሬቶች/ቦታዎች በካርታ የተደገፈ መረጃ እንዲኖራቸው ያደርጋል፣ ለኢንተርፕራይዞች እንዲተላለፍም ሥራውን ለሚመራው ተቋም ያስረክባል፤

ሐ) ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚያገለግል መሥሪያ ቦታ ስታንዳርድ ዲዛይን እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይደግፋል፣

መ) ከተሞች ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የመሥሪያ ቦታ ግንባታ ሥራ በቅድሚያ በጀት እንዲመድቡ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፣

11) **የግብርና ሚኒስቴር**

ሀ) በአግሮፕሮሰሲንግ ዘርፍ ለተሰማሩና ለሚሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ግብዓት የሚሆኑ የግብርና ምርቶችን በጥራትና በበቂ መጠን እንዲቀርብ ያደረጋል፣

ለ) ለምርት ትስስር ከፍተኛ እምቅ አቅም ያላቸውን የግብርና ንኡስ ዘርፎችና ምርቶችን መለየትና ቅድሚያ መስጠት፣

ሐ) የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራቶች/ዩኒየኖች ከአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ምርቶችን በመረከብ በማስተዋወቅና በመሸጥ የሚችሉ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።

12) **የማዕድን ሚኒስቴር**

ሀ) በማዕድን ውጤቶች ማቀነባበር ዘርፍ ለተሰማሩና ለሚሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ግብዓት የሚሆኑ የማዕድን ውጤቶች በጥራትና በበቂ መጠን እንዲቀርብ ያደረጋል፣

ለ) ለምርት ትስስር ከፍተኛ እምቅ አቅም ያላቸውን የማዕድን ምርቶችን መለየትና ቅድሚያ መስጠት፣

ሐ) የማዕድን ሥራዎች በአምራች ዘርፉ ላይ የሚያደርሱትን ተፅእኖ መከታተልና መገምገም እና ለቀጣይ መሻሻል ግብረ መልስ መስጠት።

# ክፍል አራት

## የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ሽግግርና ድጋፍ አሰጣጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲከናወን በጠንካራ ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ሊመራ ይገባል፡፡ በዚህ ክፍል የክትትልና ግምገማ ስርዓቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃቸውን ታሳቢ ባደረገ መልኩ በሚሰጥ ድጋፍና በራሳቸው ጥረት ውጤታማ እስኪሆኑ ድረስ የሚያጋጥማቸውን ችግሮችን እና የችግሮቹን ምንጭ በማወቅ የመፍትሄ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል በአስፈፃሚና ፈጻሚ አካላት በተከታታይና ቀጣይነት ባለው መልኩ **ክትትል** የሚደረግ ሲሆን መረጃ የመሰብሰብ፣ የአፈጻጸም ሂደትን የመፈተሽ እና አፈጻጸምን ከተቀመጠው ዕቅድ ጋር የማነጻጸር ስራ ይሰራል፡፡

የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማትን ለማፋጠን እና ምርትና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ፍላጎትን፣ ክፍተትን እና የዕድገት ደረጃን መሠረት በማድረግ በክትትል የተለየን ክፍተት ለመሙላት የሚደረግ **የተቀናጀ ድጋፍ** የሚሰጥ ይሆናል፡፡

የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ሽግግርና ድጋፍ አሰጣጥ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርትን መሠረት በማድረግ በየደረጃው ከዘርፉ አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረግ ውይይት ሲሆን በመድረኩ ቁልፍ የአፈጻጸም ክፍተቶች የሚለዩበትና የመፍትሄ አቅጣጫ የሚሰጥበት ይሆናል፤ አጠቃላይ የሽግግር ስራውን ውጤታማነት፣ ቅልጥፍና፣ ተገቢነት፣ ፋይዳና ዘላቂነትን ለመፈተሽ **ጠንካራ የግምገማ** ስራ የሚሰራ ይሆናል፡፡

የኢንተርፕራይዞችን የሽግግር የሥራ አፈጻጸም እንዲሁም የመስክ ክትትልና ድጋፍ ሪፖርቶችን መሰረት በማደረግ ለኢንተርፕራይዝ፣ ለባለድርሻ አካላት፣ ለፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት **በቃልና በጹሁፍ ግብረ-መልስ** የሚሰጥ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ የክትትል፣ ግምገማና ግብረ መልስ ስርዓቱ በማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ሽግግርና ድጋፍ አሰጣጥ ወቅት የተከናወኑ ተግባራትን፣ የተገኙ ውጤቶችን በመመዝገብ፣ በመተንተን እና አጠቃላይ አዝማሚያውን በማገናዘብ አፈጻጸሙ ወደታቀደለት የግብ ስኬት እያመራ መሆኑን የሚረጋገጥበት እና የታዩ ክፍተቶችን በመለየት በጋራና በተናጠል መፍትሄ የሚሰጥበትና የተገኘውን ስኬት/ተሞክሮ በመቀመር ለሌሎች እንዲተላለፍ የሚደረግበት አሰራር ነው፡፡

## 4.1 የሚከናወኑ የክትትል፣ ግምገማ እና ግብረ መልስ ስራዎች

4.1.1 በየደረጃው ያሉ ፈፃሚ አካላት የአንድ ዓመት ዝርዝር ዕቅድ የሚያዘጋጁ ሆኖ በዕቅዱ ውስጥ ለዕድገት ደረጃ ሽግግር የተቀመጡ መስፈርቶች እና የድጋፍ አሰጣጥ ማዕቀፎች መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ የተለያዩ ማንዋልዎችና ማኑዋሎች እየተፈፀሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራት በማካተት እና በየደረጃው በማፀደቅ ለኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ይላካል፤

4.1.2 በተዘጋጀው ዕቅድ መሰረት የየሩብ ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርት በየደረጃው ተዘጋጅቶና ተጠቃሎ ለኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ይላካል፣ እንዲገመገም ይደረጋል፣ የግምገማውም ውጤት ግብረ መልስ እስከ ፈፃሚ አካላት የመጨረሻው ታችኛው ዕርከን ድረስ ይሰጣል፤

4.1.3 አስቀድሞ በሚዘጋጅና በፈፃሚ አካላት እንዲታወቅ በሚደረግ ቼክሊስት መሰረት ወቅታዊ የመስክ ግምገማዎችን በማካሄድ ለተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ግብዓት የሚሆን መረጃ ይሰበሰባል፤

4.1.4 በወረዳ ወይም በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ አማካኝነት የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ የሚያመላክቱ ዝርዝር መረጃዎችን በአባሪው ቅጽ 04 በማደራጀት በክልል የዘርፉ ቢሮዎች አማካኝነት ለኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ይላካል፤

4.1.5 በማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ሽግግርና ድጋፍ አሰጣጥ የመጣውን ለውጥ መገምገምና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ማስፋት፡፡

## 4.2 ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቶች

በዕድገት ደረጃ ሽግግር የተገኘ ውጤቶችን የሚያሳዩ ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች የሚከተሉት ናቸው፡፡

4.1.1 ከጀማሪ ወደ ማደግ የዕድገት ደረጃ የተሸጋገሩ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ብዛት በንዑስ ዘርፍ፣

4.1.2 ከማደግ ወደ መብቃት የዕድገት ደረጃ የተሸጋገሩ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ብዛት በንዑስ ዘርፍ፣

4.1.3 ከመካከለኛ መብቃት ወደ ከፍተኛ የተሸጋገሩ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ብዛት በንዑስ ዘርፍ፣

# ክፍል አምስት

# መብት፣ ግዴታና ቅሬታ አቀራረብ

ይህ ክፍል የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ሽግግርና ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የኢንተርፕራይዞች እና የፈጻሚ አካላት መብትና ግዴታ እንዲሁም ተጠያቂነት ምን እንደሚመስል እና ቅሬታም ሲያጋጥም ቅሬታውን ለመፍታት የሚያስችል አሰራርን በዝርዝር የሚያሳይ ነው፡፡

## 5.1 የኢንተርፕራይዙ መብትና ግዴታ

### 5.1.1 መብት

(ሀ) በዕድገት ደረጃ አሰጣጥና አፈጻጸም ማንዋል መሰረት ለደረሰበት የዕድገት ደረጃ መስፈርቱን አሟልቶ ሲገኝ ሰርተፍኬት የማግኘት፣

(ለ) በተሰጠው የዕድገት ደረጃ እውቅና ምስክር ወረቀት መሰረት ለዕደገት ደረጃው የሚገባውን ድጋፍ በደረጃው የማግኘት፣

(ሐ) በዕድገት ደረጃ አሰጣጥ ላይ ቅሬታ ካለው የማቅረብ እና አፋጣኝ ምላሽ የማግኘት፣

### 5.1.2 ግዴታ

(ሀ) ኢንተርፕራይዙ ለዕድገት ደረጃ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ሳይደብቅ በግልጽ የመስጠት፣

(ለ) መንግስታዊ ድጋፎችን ለማግኘት ሲወዳደር ወይም ሲጫረት የተሰጠውን የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት ይዞ የመቅረብ፣

(ሐ) የዕድገት ደረጃ ሽግግር ሲያደርግ በፊት የተሰጠውን የዕድገት ደረጃ ሰርተፍኬት መመለስ፤

(መ) ኢንተርፕራይዙ በአንድ ዕድገት ደረጃ ላይ ከሁለት ጊዜ በላይ ባለበት ደረጃ ከቆየ ሰርተፍኬቱ አይታደስለትም፤

## 5.2 የፈጻሚ አካላት መብትና ግዴታ

### 5.2.1 መብት

(ሀ) የዕድገት ደረጃ ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎችን ከኢንተርፕራይዙ፣ ከባለድርሻ አካላት እና አጋዥ ሴክተሮች ጠይቆ የማግኘት፣

5.2.2 ግዴታ

(ሀ) በዕድገት ደረጃ መስፈርቶች እና በማንዋልው ዙሪያ ለኢንተርፕራይዞች መረጃ መስጠትና ግንዛቤ የመፍጠር፣

(ለ) ለሚሰጠው የዕድገት ደረጃ የሚሰበሰቡ መረጃዎችን የማጥራት በአግበባቡ የመያዝ፣

(ሐ) በዚህ ማንዋል የሽግግር መስፈርቶች መሰረት ኢንተርፕራይዞች ያቀረቡት መረጃ ተመዝኖ ነጥቦችን አሟልተው ሲገኙ በዓመት አንድ ጊዜ እንዲሸጋገሩ በማደረግ የዕድገት ደረጃ ሰርተፊኬት መስጠት፤

## 5.3 ቅሬታ አቀራረብ

5.3.1 በዚህ ማንዋል በሚሸፈን በማናቸውም ጉዳይ ቅሬታ ያለው ኢንተርፕራይዝ ወይም ጉዳዩ የሚመለተው ሦስተኛ ወገን ቅሬታ የሚያቀርብበት ጉዳይ የሽግግር ሰርተፍኬት ከወሰደበት ቢሮ ወይም ጽ/ቤት የቅሬታ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፣

5.3.2 የቢሮ ወይም የጽ/ቤት ኃላፊው የዕድገት ደረጃ ሽግግር ለሰራው ባለሞያ (ቴክኒክ ኮሚቴ) ቅሬታው እንዲታይ ይመራል፤

5.3.3 ፈጻሚው አካል የቀረበውን አቤቱታ ሰምቶ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለባለጉዳዩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ሆኖም በተጠቀሱት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ያላሳወቀው እንደሆነ ቅሬታ አቅራቢው የቢሮ ወይም የጽ/ቤት የአስተዳደር እርከን ለሚገኘው የበላይ አካል አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ ቅሬታው የቀረበለት የበላይ አካል በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠው ቅሬታ አቅራቢው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፣

5.3.4 በዚህ ክፍል ተራ ቁጥር 3 መሠረት የበላይ አካል በሰጠው ውሳኔ ላይ በሕግ ጉዳይ ረገድ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታ የቀረበበት ጉዳይ ውሳኔ በተሰጠ በ60 ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## ዋቢ ሰነዶች


1. የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ሽግግር እና ድጋፍ አፈጻጸም መመርያ (ረቂቅ) ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ 2017 ዓ.ም
2. የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ፣ የኢፌዲሪ መንግስት፣ 2016 ዓ.ም
3. የጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፖሊሲ፣ የኢፌዲሪ መንግስት፣ 2016 ዓ.ም
4. የኢትዮጵያ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፍኖተ-ካርታ፤ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ 2016 ዓ.ም
5. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ሽግግር ስትራቴጂ፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ 2016 ዓ.ም
6. የአምራች ኢንዱስትሪ የክትትልና ግምገማ ማንዋል፣ የኢፌዲሪ መንግስት፣ 2016 ዓ.ም
7. የአነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ የስልጠና ማንዋል፣ ኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ፣ 2016 ዓ.ም
8. የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 526/2015፣ ሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ 2015 ዓ.ም
9. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማት ፍኖተ-ካርታ፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ 2015 ዓ.ም
10. የጥቃቅን አነሰተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ስትራቴጂ፣ ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ 2015 ዓ.ም
11. የማምረት አቅም ጠቃቀም አመልካቾች እና የአለካክ ስልቶች ማንዋል፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ 2014 ዓም
12. የአነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዘርፍ ሪፖርትና መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አያያዝ ማንዋል፣ የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ፣ 2009 ዓ.ም
13. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ስትራቴጂ፣ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ 2004 ዓ.ም
14. የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፣ የኢፌዲሪ መንግስት፣ 1994 ዓ.ም

# አባሪዎች

## አባሪ -1፡ የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ (በሽግግር መስፈርቶች)

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዝ ዓይነት | የዕድገት ደረጃ | የሽግግር መስፈርቶች | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሰራተኛ | ጠቅላላ ሀብት | ዓመታዊ የትርፍ መጠን /ቢያንስ/ |
| 1 | አነስተኛ | ጀማሪ | 11–25 | 600,001-2,000,000 | 10% |
| | | ታዳጊ | 26--35 | 2,000,001-6,000,000 | 11% |
| | | መብቃት | 36-50 | 6,000,001-10,000,000 | 12% |
| 2 | መካከለኛ | ጀማሪ | 51-75 | 10,000,001-25,000,000 | 13% |
| | | ታዳጊ | 76- 85 | 25,000,001-55,000,000 | 14% |
| | | መብቃት | 86-100 | 55,000,001-90,000,000 | 15% |

## አባሪ -2 የኢንተርፕራይዞች የደረጃ ሽግግር መስፈርቶችና መመዘኛ ነጥቦች /ክብደት/

| ተ.ቁ | የሽግግር መስፈርቶች | ለመስፈርቶች የተሰጠ ነጥብ በመቶኛ | | | የመስፈርቶቹ ማረጋገጫ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ወደ ታዳጊ | ወደ መብቃት | ወደ መካከለኛና ከፍተኛ | |
| 1 | ***ሥራ ዕድል ፈጠራ*** | 25 | 25 | 25 | ፔይሮል |
| 2 | **ጠቅላላ የሀብት መጠን** | 35 | 35 | 35 | የተረጋጠ የኦዲት ሪፖርት |
| 3 | **ዓመታዊ የትርፍ መጠን** | 20 | 20 | 20 | የትርፍና ኪሰራ መግለጫ /የኦዲት ሪፖርት/ |
| 4 | **ምርታማነት** | 20 | 20 | 20 | |
| 4.1 | የማምረት አቅም አጠቃቀም | 5 | 5 | 5 | በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በቼክሊስት በተደገፈ የሚሰበሰብ መረጃ ውጤት |
| 4.2 | ዘመናዊ የሥራ አመራር | 4 | 4 | 4 | |
| 4.2.1 | የጥራት ቁጥጥር ስርዓት የዘረጋ | 2 | 2 | 2 | የጥራት ሰርትፍኬት |
| 4.2.2 | የንግድ ስራ ዕቅድ | 2 | 2 | 2 | የምርት/የሥራ ማሻሻያ ዕቅድ |
| 4.3 | የተኪ ምርት መጠን ዓመታዊ ዕድገት | 6 | 6 | 5 | ተኪ ምርት ስትራቴጂ ውስጥ የተካተቱ የምርት አይነት እና መጠን |
| 4.4 | የወጪ ምርት ገቢ ዓመታዊ ዕድገት | 1 | 1 | 2 | የወጪ ምርት መጠን እና ገቢ ሪፖርት |
| 4.5 | የሙያ ብቃት ምዘና | 4 | 4 | 4 | በመንግስት እውቅና ፍቃድ በተሰጣቸው የብቃትና ሞያ ማረጋገጫ ተቋማት የተሰጠ የሙያ ብቃት (ሲኦሲ) ሰርትፍኬት |
| | **ድምር** | 100% | 100% | 100% | |

**ማስታወሻ፣**

1 የኢንተርፕራይዞች የደረጃ ሽግግር የሚፈፀመው ለየዕድገት ደረጃው በድምር በመቶኛ (%) ከተቀመጠው ከጀማሪ ወደ ታዳጊ ከ75% **በላይ** ሲያገኙ፣ ከታዳጊ ወደ መብቃት **ከ80% በላይ** ሲያገኙ እና ከመብቃት ወደ ከፍተኛ **ከ85% በላይ** ሲያገኙ ይሆናል::

2 ከላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን ያሟላ ሙሉ ነጥብ የሚሰጠው ሲሆን ከከፍተኛው ነጥብ ቀጥሎ ወደታች የሚገኝ የነጥብ ውጤት **የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ ስሌት በመስራት** ይቀመጣል::

3 የወጪ ምርት ብቻ አምርተው ለገበያ የሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞች ለተኪ ምርት የተሰጠውን ሙሉ ነጥብ እና ለወጪ ምርት ገቢ ዓመታዊ ዕድገት ያገኙት ነጥብ ተደምሮ ያገኛሉ።

## አባሪ -3፡ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር ለመስራት የሚሰበሰብ ዝርዝር መረጃ (ቅጽ 01)

**ክልል / ከተማ አስተዳደር ................................** **መረጃው የተሰበሰበበት ጊዜ ............**

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | ኢንተርፕራይዙ የሚገኝበት አድራሻ | | | | | የተሰማራበት የስራ መስክ | የዕድገት ደረጃ ሽግግር መስፈርቶች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | ተፈጠረ ቋሚ የስራ ዕድል መጠን | ያለው ጠቅላላ የሃብት መጠን | ዓመታዊ የትርፍ መጠን | የማምረት አቅም አጠቃቀም | | | | |
| | | ዞን/ ክፍለ ከተማ | ከተማ | ወረዳ | ቀበሌ | ስልክ | | | | | የማምረት አቅም አጠቃቀም ልኬት | የንግድ ስራ ዕቅድ (አለ/የለም) | የጥራት ሰርትፍኬት (አለ/የለም) | የተኪ ምርት መጠን ዓመታዊ ዕድገት (በመቶኛ) | የወጪ ምርት ገቢ መጠን ዓመታዊ ዕድገት (በመቶኛ) |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |

**ቅጹን የሞላው ባለሙያ ስም --------------------**
**ፊርማ ------------------**
**ቀን -------------------**

**ያረጋገጠው ኃላፊ ስም ----------------**
**ፊርማ ---------------**
**ቀን -----------------**

አባሪ -4፡ የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር መወሰኛ ቅጽ ቅጽ 02

የኢንተርፕራይዙ ስም---------------------- የኢንተርፕራይዙ ዓይነት (አነስተኛ/መካከለኛ) ---------

ቀደም ሲል የነበረው ዕድገት ደረጃ ------------- በዚህ ምዘና ያገኘው የዕድገት ደረጃ ------------------

| ተ.ቁ | የሽግግር መስፈርቶች | ለመስፈርቶች የተሰጠ ክብደትና የተገኘ ውጤት | |
|---|---|---|---|
| | | ለመስፈርቱ የተሰጠው ክብደት (በመቶኛ) | ኢንተርፕራይዙ ያገኘው ነጥብ |
| 1 | *ሥራ ዕድል ፈጠራ* | 25 | |
| 2 | **ጠቅላላ የሀብት መጠን** | 35 | |
| 3 | **ዓመታዊ የትርፍ መጠን** | 20 | |
| 4 | **የማምረት አቅም አጠቃቀም** | 20 | |
| 4.1 | የማምረት አቅም አጠቃቀም ልኬት | 5 | |
| 4.2 | ዘመናዊ የሥራ አመራር | 4 | |
| 4.2.1 | የጥራት ቁጥጥር ስርዓት የዘረጋ | 2 | |
| 4.2.2 | የንግድ ስራ ዕቅድ | 2 | |
| 4.3 | የተኪ ምርት መጠን ዓመታዊ ዕድገት | 6 | |
| 4.4 | የወጪ ምርት ገቢ ዓመታዊ ዕድገት | 1 | |
| 4.5 | የሙያ ብቃት ምዘና | 4 | |
| | **ድምር** | 100% | |

ማስታወሻ፣

1 የኢንተርፕራይዞች የደረጃ ሽግግር የሚፈፀመው ለየዕድገት ደረጃው በድምር በመቶኛ (%) ከተቀመጠው ከጀማሪ ወደ ታዳጊ ከ75% **በላይ** ሲያገኙ፣ ከታዳጊ ወደ መብቃት **ከ80% በላይ** ሲያገኙ እና ከመብቃት ወደ ከፍተኛ **ከ85% በላይ** ሲያገኙ ይሆናል::

2 ከላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን ያሟላ ሙሉ ነጥብ የሚሰጠው ሲሆን ከከፍተኛው ነጥብ ቀጥሎ ወደታች የሚገኝ የነጥብ ውጤት **የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ ስሌት በመስራት** ይቀመጣል::

3 የወጪ ምርት ብቻ አምርተው ለገበያ የሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞች ለተኪ ምርት የተሰጠውን ሙሉ ነጥብ እና ለወጪ ምርት ገቢ ዓመታዊ ዕድገት ያገኙት ነጥብ ተደምሮ ያገኛሉ።

## አባሪ -5: ሂሳባቸውን ኦዲት ያስደረጉ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ (ቅጽ 03)

**ክልል/ከተማ አስተዳደር……………………………** **መረጃው የሚሸፍንበት ጊዜ ከ…… እስከ ……**

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | የስራ አስኪያጅ ስም | አድራሻ | | | | | የተሰማሩበት የስራ መስክ | የሚያመርተው የምርት ዓይነት | የኢንተርፕራይዙ ደረጃ<br>1.አነስተኛ<br>2.መካከለኛ | የኢንተርፕራይዙ ባለቤት/ የሚመራው | | | | ኦዲት ያስደ ረገበት ወርና ዓ.ም | ኦዲት ሲያስደርግ የደረሰበት የሀብት መጠን በብር | የኦዲት ውጤት መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዞን/ ክፍለ ከተማ | ከተማ | ወረዳ | ቀበሌ | ስልክ | | | | ወ | ሴ | ዕድሜያቸው እስከ 35 የሆኑ | አካል ጉዳተኛ | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |

ቅጹን የሞላው ባለሙያ ስም --------------------
ፊርማ ------------------
-
ቀን -------------------

ያረጋገጠው ኃላፊ ስም ----------------
ፊርማ --------------
ቀን --------------

## አባሪ -6፡ የደረጃ ሽግግር ያደረጉ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ (ቅጽ 04)

ክልል / ከተማ አስተዳደር ................................ መረጃው የሚሸፍንበት ጊዜ ከ...... እስከ ......

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | የስራ አስኪያጅ ስም | ኢንተርፕራይዙ የሚገኝበት አድራሻ | | | | | የተሰማራበት የስራ መስክ | የሚያመርተው የምርት ዓይነት | አጠቃላይ ያለው ሀብት መጠን በብር | | የኢንተርፕራይዙ ባለቤት/ የሚመራው | | | | የተሸጋገሩበት ወርና ዓ.ም | የደረጃ ሽግግር ዓይነት | | የተፈጠረ ቋሚ የሥራ ዕድል ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዞን/ ክፍለ ከተማ | ከተማ | ወረዳ | ቀበሌ | ስልክ | | | መነሻ | ወቅታዊ | ወ | ሴ | ዕድሜያቸው እስከ 35 የሆኑ | አካል ጉዳተኛ | | ከ -- | ወደ-- | ወ | ሴ | ዕድሜያቸው እስከ 35 የሆኑ | አካል ጉዳተኛ |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

ቅጹን የሞላው ባለሙያ ስም -------------------- ያረጋገጠው ኃላፊ ስም ----------------

ፊርማ ------------------ ፊርማ ---------------

ቀን ------------------- ቀን -----------------

አባሪ -7፡ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ሠርትፊኬት (ቅጽ 05)

**በ----------------ክልል/ከተማ አስተዳደር**
**የ-------------------- ቢሮ**

<u>**የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር ሠርተፍኬት**</u>

**ለ**----------------------------------------------------------------------------

ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃቸውን ያማከለ ድጋፍ ለመስጠት እንዲቻል በወጣዉ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግርና ድጋፍ አፈጻጸም ማንዋል ቁጥር ---/2017 መሰረት ኢንተርፕራይዙ ከ ——————ወደ—————— የዕድገት ደረጃ ሽግግር ያደረጉ መሆኑን በአክብሮት እናሳዉቃለን፡፡ ይህ የዕድገትደረጃ ሽግግር ሠርተፍኬት ዛሬ ————————/——————/——————ዓ. ም ተሰጥቷል፡፡

የሚመለከተው ጽ/ቤት/ቢሮ
ኃላፊ ፊርማ እና ክብ ማህተም

---------------------------

<u>**ማሳሰቢያ**</u>

1. ይህ የዕድገት ደረጃ ሽግግር ማሳወቂያ የሚያገለግለዉ ይህ ሠርተፍኬት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ሆኖ የተሰጠው ሠርተፍኬት በየአመቱ መታደስ አለበት፤ ሆኖም ኢንተርፕራይዙ በአንድ የዕድገት ደረጃ ላይ ከሁለት ዓመት በላይ ከቆየ ሰርተፍኬቱ አይታደስም፣
2. ይህ የዕድገት ደረጃ ማሳወቂያ ሠርተፍኬት በዋስትና ወይም በዕዳ ሊያዝ አይችልም፡፡